አዲስ ዘመን

አሁን

79ኛ ዓመት ቁጥር 361 ጳጉሜን 1 ቀን 2012 ዓ.ም ዋጋ 5.75

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!



በመጓመር

አዲሲቷን ኢትዮጵያ ወደ አዲስ ዘመን ማሻገር ይጠበቅብናል

ገጽ 2

የኢትዮጵያ መድን ድርጅት

ስ.ቁ 011 551 24 00
ፋክስ ቁጥር 551 74 99
ፖ.ሣ.ቁ 2545
ኢ.ሜይል
eic.mdxvs@ethionet.et
ዌብሳይት፡-
http://www.eic.com.et

አስተማማኝ አጋርዎ!

የኢትዮጵያ መድን ድርጅት

ናይል ኢንሹራንስ ኩባንያ አ.ማ
NILE INSURANCE COMPANY S.C.
Head Office Addis Ababa/Gotera/
Tel. 011 4426000
Fax 011 4426008
P.O.Box 12836
E-mail nile@ethionet.et
We serve our esteemed customers
Earnestly at Proximity with all
Insurance
business General and Long-term
YOUR SECURITY IS
OUR PRIME CONCERN!

የትግራይ ክልል መንግስት አካሂዳለሁ ያለው ምርጫ የማይጸናና ተፈጻሚነት የሌለው መሆኑን የፌዴሬሽን ምክር ቤት አስታወቀ

አዲስ አበባ፡- የትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት፣ አስፈፃሚ አካላት እና የምርጫ ኮሚሽን ምርጫን በሚመለከት ያወጣው አዋጅ፣ ያሳለፏቸው ውሳኔዎችና የፈፀሟቸው ተግባራት ከሕገ መንግስቱ ጋር የሚቃረኑ በመሆናቸው በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 9(1) መሰረት እንዳልተደረጉ የሚቆጠሩ፣ የማይፀኑ እና ተፈፃሚነት የሌላቸው መሆኑን የፌዴሬሽን ምክር ቤት በሙሉ ድምጽ የመጨረሻ ውሳኔ ማሳለፉን አስታወቀ።የፌዴሬሽን ምክር ቤት በትግራይ ክልል እየተካሄደ ያለውን የምርጫ እንቅስቃሴ በተመለከተ የምክር ቤቱ የህገ መንግስት ትርጉምና የማንነት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ባቀረበለት የውሳኔ ሀሳብ ላይ ትናንት ከመከረ በኋላ የውሳኔ ሀሳብ አቅርቧል።

በኢትዮጵያ ስድስተኛው ሀገራዊ ምርጫን በተመለከተ የኮቪድ-19 ወረርሽኝ መቀስቀሱን ተከትሎ የኢትዮጵያ ብሄራዊ ምርጫ ቦርድ የተለያዩ ምክንያቶችን በማስቀመጥ ምርጫውን ማካሄድ እንደማይችል

የትግራይ ክልል ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

ማረሚያ

በትናንት እትማችን በመጀመሪያው ገጽ “የኢትዮጵያዊነት አስተሳሰብ አሁን ላይ ፀጥ እንዳለ ባህር ሆኗል” በሚል በተስተናገደው ዜና አቶ አንዷለም አራጌ የኢዜማ ምክትል ሊቀመንበር የሚለው በስህተት ስለሆነ የኢዜማ ምክትል መሪ በሚል ተስተካክሎ ይነበብ ። ለተፈጠረው ስህተት አዲስ ዘመን ይቅርታ ይጠይቃል

በውስጥ ገጾች

አገራዊ ጉዳዮችን የዘነጉ ፊልሞቻችን

ገጽ 7



«ኢትዮጵያ ከመቼውም በላይ የተስፋ አየር መተንፈስ የሚያስችላት አሰላሳዮችን ትፈልጋለች»

- ኡዝታዝ ያሲን ኑሩ

ገጽ 8

አዳማ ቆርቆሮ ፋብሪካ ADAMA STEEL FACTORY



0940 505050/0940 606060/0940 909090/0940 808080/0920 656565

በመደመር አዲሲቷን ኢትዮጵያ ወደ አዲስ ዘመን ማሻገር እንደሚጠበቅብን የሀይማኖት መምህራን አሳሰቡ

ጽጌረዳ ጫንያለው

አዲስ አበባ፡- እስካሁን የተከማቹ ችግሮችን ለመጪው ትውልድ ላለማውረስ ጠባሳ የሌለው ሰላምን በመደመር መንፈስ አጥፍቶ አዲሲቱን ኢትዮጵያ ወደ አዲስ ዘመን ማሻገር እንደሚገባ የሀይማኖት መምህራን ገለጹ።

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን የውጭ ጉዳይ መምሪያ ሃላፊና መምህር ዳንኤል ሰይፈሚካኤል ለአዲስ ዘመን ጋዜጣ እንደተናገሩት፤ ትውልድ የተሻለች ኢትዮጵያን ይፈልጋል። ለዚህ ደግሞ ማንኛውም ዜጋ ባለፉት ዓመታት የተመዘገበውን መልካም የፖለቲካ፤ ኢኮኖሚና ማህበራዊ ድሎችን ማስጠበቅና ማስፋት ይጠበቅበታል።

የተሠሩ ስህተቶችን ማረምና መፃኢ ተስፋውን ማስተካከልም የውዴታ ግዴታው ነው ያሉት መምህር ዳንኤል፣ መጪው አዲስ ዓመት ብሩህና አገር አሻጋሪ እንዲሆንም ከቂም፤ ከበቀልና ጥላቻ፣ ሲከፋፍልን ከኖረው ክፋት መላቀቅ በምትኩ መቀባበልና መተጋገዝን ማጎልበት እንደሚገባ አመልክተዋል።

ግለሰባዊ ነጻነትና ማኅበረሰባዊ ደኅንነት መላበስን ገንዘብ በማድረግ ነገን ማየት እንደሚያስፈልግ የጠቆሙት መምህር ዳንኤል፤ በተለይ በሀሳብ ልዕልና የሚያምንና ምክንያታዊ የሆነ ዜጋን መፍጠር ላይ ዛሬ መረባረቡ የግድ ነው ብለዋል። ኢትዮጵያ ብዙ በጎ እሴቶች የሞሉባት በመሆኗም ይህንን መጨመር እንጂ ወደ ዜሮ ድምር የሚያስገባትን ማምጣት እንደሌለባት ጠቁመዋል።

የሀይማኖትና የአመራር መምህሩ ኡስታዝ ያሲን ኑሩ በበኩላቸው፤ ለአገራችን ሁላችንም እናስፈልጋለን፤ ከመካከላችን የማያስፈልግ ነገር የለም ፤ በዚህም ኢትዮጵያን የሚያስፈልጋቸው ከክስተትነቱ ይልቅ ሂደትነቱ ያመዘነ፣ ከንግግር ይልቅ ተግባር ላይ ያተኮረ፣ ከእኔነት ይልቅ እኛነት ላይ የተመሰረተ ጽኑሰ ሀሳብ ነው ።

" ብሔሮች ፤ብሔረሰቦችና ሕዝቦች በአንድነት



መምህር ዳንኤል ሰይፈሚካኤል



ኡስታዝ ያሲን ኑሩ

ሆነው ያለውን ታሪካዊ፣ ባህላዊ፣ ጥበባዊና ኢኮኖሚያዊ ጸጋ እየደመሩ ፤ የሁሉንም የያዘችና በሁሉም የምታዜጥ አንዲት ታላቅ ኢትዮጵያን መፍጠር የሚችሉ መሆናቸውን ማሳየት ያስፈልጋል " ብለዋል።

ሁሉም ሰው ለሌላው ሊሰጥና ሊያበረክት የሚችለው ነገር እንዳለው የሚያነሱት መምህሩ፤ በአዲስ አመት ለአገራችን ልናበረክትላት የምንችለው ነገር በጎ ፈቃዳችንን፣ መልካም ንግግራችንንና ሰናይ ግብራችንን ነው ብለዋል ። የራሳችንን የተሻለ ማንነት በመገንባት ወደ ሌሎች በመድረስ ሀገራችን ብሩህ ተስፋን እንድታይ ማድረግ እንደሚጠበቅብን አመልክተዋል ፤ ባለመደመር ጦስ ከሚመጣ መከፋፈልና መጠፋፋት መዳናችን ማሳያም ይህው መሆኑን አስታውቀዋል።

በተለይ አግላይነትና ሌላውን ጥላሸት ከመቀባት እርቀን አገራችንን ወደታላቁ ልዕልና ስናሻግራት ስጦታዋ መልካም ይሆንላታል ብለዋል። ለራሳችን ካለን በጎነትና መልካም እይታ ቀንሰን ለሌሎች መስጠት ስንጀምርም እንዲሁ አገራችን በስጦታው ትደሰታለችና አዲሲቷን ኢትዮጵያ በአዲስ ዓመት ይህንን እናበርክትላት ሲሉም ጥሪ አቅርበዋል።

በኢትዮጵያ ነባራዊ ሁኔታ ያልተባበረና ያልተሳሰበ ሕዝብ የውስጥንም ሆነ የውጪውን ችግሮቹን በብቃትና በንቃት መመከት ፈጽሞ አይቻለውም የሚሉት ኡስታዝ ያሲን፤ ማበር ምን ያህል ዋጋ እንዳለው ዓድዋ አስገንዝቦን አልፏልና አሁንም በመደመር መንፈስ ጠባሳ የሌለው ሰላምን በአገር ላይ ለመፍጠር መታትር እንደሚያስፈልግ ተናግረዋል።

አሁን በእጃችን ያለችው አዲሲቷ ኢትዮጵያ ታላቅ መሥዕዋትነት የተከፈለባት የጋራ ትግላችን ውጤት ናት እሷን አሳልፎ ለጥፋት መስጠት የታሪክ ተወቃሽ ያደርጋል ያሉት መምህሩ ኡስታዝ ያሲን፣ በመተባበር አዲስ ዘመንን ለአዲሲቷ ኢትዮጵያ ማምጣት ተገቢ መሆኑን አመልክተዋል ።

‹‹ ቂምና ቁርሾ በበጋው ንፋስ፤ በክረምቱ ጎርፍ ይደፍ ››

- አባገዳ ጎበና ሆላ

በጋዜጣው ሪፖርተር

አዲስ አበባ፡- ቂምና ቁርሾ በበጋው ንፋስ ፣ በክረምቱ ጎርፍ ይለፍ። በአዲሱ ዓመት መልካም መልካም ባህሎቻችንን ደምረን፣ ስህተቶቻችንን አርመን ለሀገራችን አንድነት እና ልማት በጋራ መቆም አለብን ሲሉ አባገዳ ጎበና ሆላ አሳሰቡ።

የኦሮሞ አባ ገዳዎች ህብረት ጸሐፊና የቱለማ ገዳ አባገዳ ጎበና ሆላ በተለይ ለአዲስ ዘመን እንደተናገሩት፣ አዲሱን ዓመት ስንቀበል እንደ ኢትዮጵያዊም ሆነ እንደ ኦሮሞ በቂምና በጥላቻ የከረመ ቁስልን እያከክን ሳይሆን በማወቅም ሆነ ባለማወቅ ለጠፋው ጥፋት ይቅር በመባባል ነው።

አዲሱን ዓመት የምንቀበለው በቂምና በቁርሾ ሳይሆን ለሀገርና ለህዝብ አንድነት መልካም መልካም ነገሮችን እያሰብን የነበሩ ችግሮችንም በይቅርታ በማለፍ መሆኑን ጠቅሰው፣ በጊዜያዊ ጥቅም ለፖለቲካ ትርፍ ተብሎ የሚፈጠር ግጭትን በማቆም መሆን እንደሚኖርበትም አመልክተዋል።

የገዳ ስርዓት ቂምና ቁርሾ በበጋው ንፋስ ፤ በክረምቱ ጎርፍ ይለፍ የሚል ነው ያሉት አባገዳ ጎበና፣ ይቅርታ በኢትዮጵያውያን ዘንድ የተለመደ፣ በኦሮሞ ማህበረሰብ ደግሞ እጅግ የተከበረ ነው ብለዋል። « ይቅር እንባባል ማለት ያጠፋነው ትንሽ ነው፣ የሚቀረን ብዙ ነው፤ ከዘመን ዘመን፣ ከክፍለ ዘመናት ከፍለዘመናት ቁርሾ እና ቁስል እያከክን ከምንጠላለፍ ያለፈውን ለታሪክ ትተን በአንድነት፣ በመተሳሰብና በፍቅር እንኑር ማለት ነው » ሲሉም ተናግረዋል።

አባገዳ ጎበና እንዳሉት ፤ በኦሮሞ ባህል የተቀያየመ ሰው ከጎረቤት፣ ከቤተሰብ፣ አልፎ ተርፎ ከተቀያየመው ብሄር ብሄረሰብ ሁሉ ይቅር ብሎ ይቅርታ ይጠያየቃል። የገዳ ስርዓትም የሚያስተምረውና የሚተገብረው ይህንን ነው። ይቅርታ ከስህተታችን ተራርመን ለወደፊቱ ፍቅር እንድንሆን የምንሄድበት መንገድ ነው።

ይቅርታ ትልቅ ዋጋ እንዳለው አንዱ ማሳያችን በኢትዮጵያና ኤርትራ መካከል የነበረውን ቅራኔ እንዴት እንደተፈታና እንዴት ወደሰላም መንገድ እንደመጣን ያየንበት ነው ያሉት አባገዳ ጎበና፣ የነበረውን የሰላም መደፍረስ በይቅርታ ተላልፈን ጥሩ ወዳጅነት መስርተናል። በዚህ መሀል ብዙ ጥቅሞች ተገኝተዋል፤ ይሄ የይቅርታን ትልቅነት ማሳያ እንደሆነም አስታውቀዋል።

ሀገራችንን በልማት የምናሳድገው ፣ አንድነቷ ተጠብቆ ህዝብ በሰላም የሚኖረው በህግ የሚፈለገው በህግ እየተጠየቀ፣ በይቅርታ መተላለፍ ያለበትም በይቅርታና በምህረት መተላለፍ ከተቻለ ብቻ ነው ያሉት አባገዳው፣ ይቅርታ በየትኛውም ዓለም ያለ፤ በሀገራችንም መንግስት በማረሚያ ቤት ለሚገኙ ሰዎች ይቅርታ እያደረገ እንዲፈቱ የሚያደረግበት ስርዓት



አለ። ስለዚህ የይቅርታ ጉልበቱ ጠንከራ መንገዱም ረጅም ነው ብለዋል።

ለሀገር ሰላም ለህዝቦች አንድነት የሀይማኖት አባቶች፣ የሀገር ሽማግሌዎች፣ ታዋቂ ሰዎች እና አባገዳዎች ትልቅ ሀላፊነት እንዳለባቸው ገልጸው፣ አዲሱ ዓመት በመከባበር፣ በመተሳሰብ፣ ለሀገራችን ብልጽግና በጋራ የምንሰራበት ሊሆን ይገባል ። ለዚህ ደግሞ ይቅርታ ትልቅ ቦታ እንዳለው አመልክተዋል።

ርዕሰ አንቀፅ

በመደመር ወደ ብልጽግና እንሻገር

ኢትዮጵያዊያን በአንድነት ገመድ የተጋመድን ህዝቦች ነን። የብሄር፣ የቋንቋ፣ የሀይማኖት ልዩነት ሳይፈትነን ብሄር ብሄረሰቦች በአንድነት በመቆም ደማቅ የጋራ ታሪኮችን ሰርተናል። ለነጻነታችን በጋራ ቆመናል፤ የውጪ ወራሪ ሀይልን አርበድብደን አሸንፈናል።

በአድዋ፣ በዶጋሊ፣ በመተማ፣ በባድመ እና ዛላንበሳ ኢትዮጵያውያን ብሄር ብሄረሰቦች በጋራ ደማቸውን አፍስሰውና መተኪያ የሌላትን ህይወታቸውን ገብረው ታሪክ ሰርተዋል። ዛሬም ድረስ የምንኮራበትን ነፃነቷ የተከበረ፣ ሉዓላዊነቷ የተረጋገጠ የአፍሪካ ኩራት የሆነች ሀገር አስረክበውናል። ኢትዮጵያውያን ስማችን በዓለም ላይ በታሪክ መዝገብ ከሰፈረበት አንዱ ይሄው የአልበገር ባይነት የድል አጥቢያ ኮከብ መሆናችን ነው።

ኢትዮጵያ የብዙ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች አገር ናት። እነዚህ ህዝቦች በልዩነት ውስጥ አንድነትን፤ በአንድነት ውስጥ ልዩነትን አቻችለው በፍቅር በሰላም ኖረናል። ይሁን እንጂ ዛሬ አንዴ በፖለቲካ ርዕዮተ ዓለም ልዩነት፣ ሌላ ጊዜ በብሄር ብሎም በሀይማኖት ሊያጋጩ፣ ሊለያዩንና ሊበታትኑን የሚጥሩ ጠላቶች በውስጣችን እየተፈታተኑን ይገኛሉ።

ይሄ የትም የማይደርስ ፣ ይሞከራል እንጂ የማይጨረስ ከንቱ ምኞት ነው። ኢትዮጵያውያን ከዚህም ቀደም ብዙ ችግሮችን አሳልፈናል። በየዘመናቱ ያጋጠሙንን ጨቋኝ ስርዓቶች ሁሉ በጥበብና በዘዴ አስወግደናል። አሁንም ሊበታትኑን ለሚፈልጉት ፊት የማንሰጥ፣ እጅ የማንጠመዘዝ መሆናችን ግልጽ ነው።

አሁንም የእምነት፣ የብሄር፣ የፖለቲካ ርዕዮተ ዓለም ልዩነት የሚያለያዩን አይሆኑም፤ ይልቁኑም በልዩነታችን ውስጥ አንድነታችንን እያየን እና አገራችንን እያስቀደምን ወደፊት አሻግረን እንመለከታለን። አዲሱ ዓመት 2013 ልዩነቶቻችንን የምናጠብበት፣ ለመደማማጥ፣ ለመነጋገር ለውይይት ራሳችንን ከፍት የምናደርግበት ዓመት እንደሚሆን ተስፋ እናደርጋለን።

ኢትዮጵያውያን ቀደም ሲል የሚያጋጥማቸው ችግሮች ነበሩ። አሁንም አሉ፤ ወደፊትም ይኖራል። ችግሮች ሲገጥማቸው ታዲያ የውጪውን ወራሪ በጦርነት፣ በዲፕሎማሲ ሲፈቱ የውስጡን ደግሞ በጥበብ ይመልሳሉ። አሁንም ጥሩ ጥሩ ለሀገር ለወገን የሚበጁ ችግር መፍቻ መንገዶቻችንን ተጠቅመን ችግሮቻችንን መፍታት አለብን።

የሚያምርብን መጥፎ መጥፎውን ቀንሰን፤ ደግ ደጉን ደምረን ህዝባችንን ወደፊት፤ ሀገራችንን ወደ ብልጽግና ማሻገር ነው። በአገራችን ፌዴራላዊ ሥርዓት ከሰፈነ በኋላ በብዙ መስክ መሻሻሎች ቢታዩም የህዝቦች ጥያቄ ግን አሁንም ድረስ በሚፈለገው ደረጃ ሳይመለስ ቆይቷል።

የብሄር ብሄረሰቦች መብትና እኩልነት ተከብሯል፤ ክልሎች ራስን በራስ ማስተዳደር ችለዋል ቢባልም ይታዩ የነበሩ ጣልቃ ገብነቶች፣ ሙስና እና ኢ-ፍትሃዊነት ህዝቦችን ያንገሸገሹ ነበሩ። ይህም ነው በሀገራችን ለውጥ እንዲመጣ ምክንያት የሆነው።

የመጣውን ለውጥ ወደፊት መውሰድ፣ ጥንካሬውን ማጎልበት ድክመቱን ማረም ደግሞ ከእያንዳንዳችን የሚጠበቅ ነው። የመደመር እሳቤ መነሻ ዓላማ ለአገር በቀል ችግር አገር በቀል መፍትሄ መፈለግ ነው። በአገራችን ኢትዮጵያ ያሉ መልካም የፖለቲካ፣ ማህበራዊና ዲፕሎማሲያዊ ድሎችን ጠብቆ ማስፋት ነው።

የተሰሩ ስህተቶችን ማከም፣ ማረምና እርምጃ መውሰድ አስፈላጊ ነገሮች መሆናቸው አጽንኦት ይሰጣል። ህብረ ብሄራዊ አንድነት፣ የዜጎች ከብርና ብልጽግና የመደመር ግቦች እንደሆኑም ያስቀምጣል።

የሚፈጠረው አገራዊ አንድነትም የብሄር ብሄረሰቦችን ማንነት፣ ባህልና ቋንቋ እንደጸጋ የሚውስድ እንጂ የሚደፈጥጥ እንዳልሆነ ቁልጭ አድርጎ ያስቀምጣል። ከዚህም በላይ ዜጎች በአገራቸውም ሆነ በውጭ አገር ከብራቸው ተጠብቆ መኖር እንደሚገባቸው አጽንኦት ይሰጣል። የመቆራቆዝና የመነቋቆር ምንጩ ድህነት በመሆኑ ድህነት የሚወገደው ብልጽግናን በማስፈን ነው።

የኢትዮጵያ ትልቁ የፖለቲካ ስብራት ጭቆና ነው ብሎ የሚያስቀምጠው ፍልስፍናው መፍትሄው ደግሞ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መገንባት መሆኑንም ያስቀምጣል። ለፖለቲካ ሳይሆን ለአመራር ብቃት ትኩረት የሚሰጠው ይህ እሳቤ ብቃትና ውክልናን አመጣጥኖ መምራት ተገቢ መሆኑንም ያሰምርበታል።

እንደ ከዚህ ቀደሙ ከአንድ ቦታ በሚመነጭ ሳይሆን ተቋማት ባህሪያቸውን ያማከለ ሪፎርም ማድረግ እንዳለባቸውም ይመከራል። ከኢኮኖሚ ዕይታም አንጻር መደመር ዛሬ ላይ ያለንን መሰብሰብ ትናንት ከነበረው በጎ ሥራ በማከማቸትና በማካበት ሥርዓት ማስያዝ በሚሉ ቁልፍ መርሆዎች ይመራል። በዚህም ያለፉትን ጊዜያት ድሎች ጠብቆ ማስፋት፣ ስህተቶችን ያለምህረት ነቅሶ ማረም፣ የመጻኢውን ትውልድ ዕድል ስኬታማና ብሩህ ማድረግን እንደ መርህ ልንከተል ይገባል።

አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

ዋና አዘጋጅ

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

አድራሻ

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

ምክትል ዋና አዘጋጅ

አልማዝ አያሌው
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-10

አዘጋጆች

ተገኝ ብሩ
ጽጌረዳ ጫንያለው
አብረሃም ተወልደ
ዳግም ከበደ
ሞገስ ፀጋዬ

አምደኛ

የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ

ኢሜይል - epapromotion@press.et ስልክ - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-156-98-62

የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-65

የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ

ስልክ - 011-1-26-43-39

ማከፋፈያ

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70

አንወራወር

ደህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው። በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም።

ታርቀን ወደ 2013

ተገኝ ብሩ

አገር በልጆቿዋ ትነግሳለች፤ በአብራኳ ከፋዮች ትከብራለች፤ በሕዝቦቿዋ መተሳሰብና አንድነት ትፀናለች። ያቺ የፀናች ብርቱ አገር ደግሞ ለልጆቿዋ መከታ ለፍሬዎችዋ ጥላ ለአብራክዋ ከፋዮች ደጀን ሆና ትቆማለች። ያኔ ሕዝብ አገሩን እጅጉን ይወዳል። አገሩን የወደደ ዜጋ ስለአገሩ ምንም ይሆናል። ስለ ወገኑ እራሱን አሳልፎ ይሰጣል። ስለ አገሩ ብሎ ስሜቱን ይገታል። ስለ እናት ምድሩ ብሎ በይቅር ባይነት በደሉን ይረሳል።

በፍቅር እርስ በርስ የተጋመደ፤ በመቻቻል አንዱ አንዱን ይዞ እልፍ አመታትን የተሻገረ ሕዝብ የትስስሩ ምክንያት የአብሮነቱ ሚስጥር መቻቻሉ፤ ይቅር መባባሉ እንጂ ሌላ ምንም ሊሆን አይችልም። በጉዞው የገጠመውን ልዩነትና ተቃርኖ ይቅር በመባባል ፍቅሩን አፅንቷል። ዛሬም ይህ ሕዝብ ኃያልነቱን ለማረጋገጥ ለፍቅር ዝቅ ማለት ግድ ይለዋል። ያለፈውን ታሪኩን መማሪያ አድርጎ የወደፊቱን በማለም በይቅርታ መሻገር ይገባዋል።

ለእርሱ ዝቅ ሲሉ የከፍታዎች ሁሉ ከፍታ ላይ የሚያስገኘው ፍቅር መገኛው ንፁህ ልብ ነው። ልብ እንዲፀዳ ደግሞ ቂምን ከውስጡ ማስወገድ ይገባል። ልብን የሚያፀዳው ፀዳል ደግሞ ይቅርታ ነው። ፍቅር መፍትሄዎች ሁሉ የሚጎናፀፉበት ከፍታ ነው። መወጣጫው መንገድ ደግሞ ይቅርታ። ይቅር ለማለት አገር መውደድ በዚያ ውስጥ ደግሞ ስለ አገር ብሎ ይቅር ማለትን ይወልዳል።

ይቅርታ ከስህተት የሚመልስ መንገድ እንደመሆኑ መንገዱን ቀድሞ መጥረግ ይገባል። በእኛነታችን ውስጥ በጎ እሳቤ የሚፈጥር አዎንታዊ አስተሳሰብ የሚመነጨው ከራስ ጋር ባለ ሰላም ውስጥ ነው። ያንን ሰላም ለመጎናፀፍ ደግሞ ከሌላ ጋር እርቅን ከመፍጠር በፊት ከራስ ጋር መታረቅ ይገባል። ሰው ቀድሞ ከራሱ ጋር ከታረቀ አስታራቂ የሆነውን መልካም ነገር ማሰብ አይከብደውም።

ሁሌም ከራሳችን ጋር ያለመግባባት የረጋ ስሜት ያላብሳል። ይህ መስከን ነው ሰላም የሚያደርገን። ያ ሰላም ደግሞ ከራስ አልፎ ለሌላም ይተርፋል። ያኔ ሌላን ይቅር ማለት ከሌላ ጋር መታረቅ ይቀለናል። በተናወጠ ማንነት ውስጥ መስከንን መጠበቅ እንዴትስ ይቻላል? ያልሰከነ ግለሰብ የረጋ ማህበረሰብ መሀል ላይ ተገኝቶ መፍትሄን የሚወልድ በጎ ሀሳብ መፍጠር ይሳነዋል።

ከስህተት ለመተራረም መመካከር ወሳኙ ነጥብ አይደል? ተቀራርቦ ለመነጋገር ደግሞ ያለፈን ትቶና የፊትን አልሞ ከልብ ይቅር ማለትን መልመድ ይገባል። አንዱ ካንዱ ጋር የመመካከር ዙፋን ላይ ለመቀመጥ ከራሱ ጋር መከሮ መጨረስ ከራሱ ጋር መስማማት ማስቀደም ግድ ይለዋል።

ስንቶቻችን ነን አገር የምትጠብቅብን ኃላፊነት በወጉ የተወጣን? ከእርስዋ ከመጠበቅ ይልቅ እርስዋ ከእኛ የምትጠብቀውን የሰጠን? ስንቶቻችን ነን አገር ፀንታ እንድትቆም ሕዝብ ከተጋረጠበት ችግር እንዲላቀቅ የተጋን? ኧረ ምን ያህሎቻችን ነን ከእኔ ይልቅ አገሬ ቀድማ ትለወጥ ያልን? በልበ ሙሉነት ለአገሬ ይህን አድርጌያለሁ የምንለው ብርቱ ተግባራችን የቱ ጋር ነው። ይህንን ያደረገ ስለ አገሩ እራሱን የሰጠ እጁን ያውጣ። እሱ የምር ነፃ ነው። ታዲያ አገራችንን እናታችን ይቅርታ መጠየቅ አይገባንምን?

እኔ ግን ተንበርክከን ታላቁን ይቅርታ መጠየቅ የሚገባን ለእናት ምድራችን መሆን እንዳለበት ይሰማኛል። አገራችን የምትፈልገውን ያህል ከልጆቿዋ የሚገባትን መወጣት የተሳነን ነንና ይቅርታ ልጠይቅ ይገባል። እኔ እንደ ዜጋ አገሬ፤ እምዬ፤ እናቴ እንድትቀናልኝ የሚጠበቅብኝን አልተወጣሁም ይቅር በይኝ እላለሁ።

እኛ የዚህች አገር ፍሬዎች፤ የዚህ ምድር ቡቃያዎች እናት ምድራችን የምንወድ ከሆነ ስለስዋ መልካም የምንመኝ የስዋን ለውጥ ማየት የምንናፍቅ ይቅር መባባል ግድ ይለናል። ወገን ቀድመን ይቅርታ መጠየቅ ያለብን ተንበርክከን አገራችንን ነው። የእናትነት ያህል ክብር፤ የሚገባትን ያህል ፍቅር፣ የኃያልነትዋ ያህል ውዳሴ አልቸርናትምና አገራችንን ይቅርታ ልንጠይቅ ይገባል።

አገሬ ይቅር በይኝ የሚል ወኔን ተላብሰህ አገርህንና በአገርህ ውስጥ ያሉ ወገኖችህን ትደርሳለህ። አገር አድርገው ያቆሟትን ልጆችዋን ይቅር ትላለህ። አገርህን በትክክል ስተረዳ እስዋን ስትወድ ለአገርህም ማበርከት ያብህን ስታስብ ምንም አለማድረግህ ይገባህና አገሬ ይቅር በይኝ ትላለህ። ያኔ ሕዝብህን ወገንህን የበደልከው ምን ያህል መሆኑ ይገለፅልህና ለይቅርታ ልብህ ክፍት ይሆናል።

ይቅርታ የፍቅር መንገድ የመሆኑን ያህል ቂም ፍቅርን ከልብ የሚያጠፋ ውስጥን የሚያጠለሽ ጥላ ነው። ስለዚህ ቂምን ከውስጣችን እንጠፍጥፈን ፍቅርን ወደኛ የሚያቀርበውን ይቅርታ እንልመድ። በአንድ ላይ ዘመናትን ያለፍን በጋራ ችግርና ደስታን የተጋራን ከሚነጥል ይልቅ ያጋመደን ብዙ ነገር አለና እንደ አገር ይቅር ተባብለን ወደ ፊት በጋራ እንራመድ። ቂም በቀሉን ትተን ስለ አገር ብለን ይቅር መባባልን እንውደድ። በይቅርታ ወደ ፍቅር ቀርበን አንድ ላይ ወዳለምነው ግብ እንሻገር።

ይቅር ብለን መታረቃችን ከልብ ሆኖ ግንኙነታችን ይሰምር ዘንድ ቂምና ቁርሾ እንተው። ለእርቅ ዝግጁ ሆነን መታረቃችን የምር አድርገን የጋራ ጉዞ እንጀምር። ይቅር ባይነት ለምንወዳት አገራችን የሚበጅ ነውና ይቅርታና ይቅር ተባብለን የምንታረቀው እርቅ ቀድመን ከራስ ብሎም ከማህበረሰባችን ሰፍቶም ከአገር ጋር መሆን ይገባዋል።

ለእርቅ የሚሆን ንፁህ ልብ እንላበስ። የተጣላነው ከራሳችን ከወገናችን አብሮን ገበታ ቀርቦ ምግብ ከሚጋራን አብሮ አገር ለማስከበር እራሱን ለኛ ከሰጠ ወገናችን ጋር ነው። ከራስ ጋር እንዴት ተጣልቶ ይሆናል። በሕይወት ሳሉ ከራስ ጋር መጣላት የመሰለ የከበደና ትልቅ ፈተና የለም። ከራስ ጋር ያለ ስምምነት መኖር ምንኛ ከባድና የከፋ ስለመሆኑ መገመት ከባድ አይደለም።

አስታራቂ የሌለው የማያቆም ግጭት በራስ ውስጥ የሚፈጠር የመሸናነፍ ፉክክር። ከልክ በላይ ሕመም የሚፈጥር መጣረስ፤ ለሽምጋይ የሚችግር ተቃርኖ፣መጨረሻው ተያይዞ መጠፋፋት ነው። ብቻ መቆም እኮ ከባድ ነው። ተጋግዞ ተደጋግፎ መጓዝን፣ አብሮ ሆኖ ማለምን ፣ በአንድነት መገስገስን የሚያላብሰው ጥንካሬና ብርቱነት እንዴት ሳይገባን ቀረ።

ይቅር ባይ ትውልድ ለፍቅር እጁን የሰጠ ነውና የሰመረ ስምምነት ያለው አካባቢያዊ ሁኔታውን በመልካም ነገር መለወጥ አይከብደውም። ከእርስ በእርስ ግንኙነትና ጉድኝት ስምረት ቀድሞ ከራሳችንና ከአካባቢያችን ጋር የምንፈፅመው መልካም ግንኙነት ትልቅ ሚና አለው። ባለፈ ነገር በመማር የወደፊቱ አስቦ ይቅር የሚል ማህበረሰብ ለችግሮቹ መፍቻ መፍትሄ ማመንጨት ይቀለዋል።

እንደ ማህበረሰብ እያንዳንዳችን በበጎ እሳቤ ላይ ለመዘውተር አተያያችን መቀየር ይገባናል። ከገዘፈ ክፉ ነገር ጥቂትም ብትሆን ጥሩ ማጉላት መላመድ ይገባናል። እጅግ ከሰፋ ጭለማ ውስጥ በጭላንጭል የምትታይ ሻማ እንደ ትልቅ ተስፋ ቆጥሮ በጎውን ማለም መላመድ ይገባናል።

የማህበረሰባችን ሁለንተናዊ አተያይና በጎ የሚባሉ እሴቶች ዛሬ ላይ የት ገቡ? የሚያሰኘን አጋጣሚ የሚፈጠረው እኮ ከእርስ በእርስ መተዛዘንና መግባባት በፊት ለራስ ክብር መስጠትና ከራስ ጋር እርቅ መፍጠር ስለራቀን የሚያግባቡን እና የሚያስታርቁን እውነቶች አለመለየታችን ነው። ዛሬ ይህንን መለወጥ የሚገባን ጊዜ ነውና የተበደለ በዳዩን ይቅር የሚልበት ተበድሎም የሚያሸንፍበት ወደ ፍቅር የሚጣራበት ጊዜ እናድርገው። ያኔ ሁላችንም ይቅርታው ያስታርቀናል። ወደ ፍቅርም ይመራናል።

የምር ይቅር አለማለታችን ቂምና ቁርሾ ማሰባችን የእርስ በርስ ግንኙነታችን ያዛባዋል፤ ማህበራዊ እሴታችንን ይሸረሽረዋል። እያንዳንዳችን እራሳችንን ለማቅናት ውስጣችንን ለማንፃት ዝግጁ መሆን ይገባናል። ውስጣችን ጥሩ የሆነ ስሜት ሳይሰማው ስለአካባቢያችንን ጥሩ መሆን ሊያስጨንቀን አይችልም። ስለ ግላችን የሚሰማን መጥፎ ስሜት አካባቢያዊ ጉዳዮቻችን ላይ መጥፎ ገፅታን ይፈጥራል።

ዛሬ ላይ አብረን በጋራ የምንጋፈጣቸው አስቸጋሪ ሁኔታዎች ሲያሻግሩን የቆዩ እሴቶቻችን መለዘብ የጀመሩትም በዚሁ ሰበብ ነው። ይቅር ማለትን ስለከበደን ይቅር የሚል እርቆናል። ከራሱ ጋር እርቅ ፈጥሮ መስከን ላይ የደረሰ ማህበረሰብ ውጫዊ ማንነቱ ላይ በጎነትን ይላበሳል። አበቃሁ !ቸር ይግጠመን።

ሰላም ለሁላችሁ ወዳጆቻችን፤ ዛሬ ስለ ጤና ጉዳይ ነው የምንጫወተው። ጤና ማለት ሰው ሲታመም ብቻ የሚታሰብ ነገር አይደለም። ጤና ማለት ሰው ሳይታመምም ቢሆን ሰውነቱን ተንከባክቦ የሚኖርበት ሕይወት ነው። ብዙ ሰዎች ግን ሰውነታቸውን ከመንከባከብ ይልቅ ሰውነታቸው እስኪታመም ድረስ ዝም ይላሉ። ከዚያ በኋላ ነው ሐኪም ቤት የሚሮጡት። ይህ ግን ትክክለኛው መንገድ አይደለም።

ጤናማ ሰውነት እንዲኖረን በመጀመሪያ ማድረግ ያለብን ነገር ንጹህ ውሃ መጠጣት ነው። ሰውነታችን ከሰማንያ በመቶ በላይ ውሃ ነው። ውሃ ሲጠማን ብቻ ሳይሆን በቀን ቢያንስ ስምንት ብርጭቆ ውሃ መጠጣት አለብን። ሻይ፣ ቡና እና ለስላሳ መጠጦች ውሃን አይተኩም። ከመጠን በላይ ስኳር ያላቸው መጠጦች ደግሞ ለስኳር በሽታ እና ለልብ ህመም ያጋልጣሉ።

ሁለተኛው ነገር ምግብ ነው። ብዙ ሰዎች ጣፋጭ ምግብ ስለሚወዱ ብቻ ብዙ ይበላሉ። ነገር ግን ከመጠን በላይ መብላት ውፍረት ያመጣል፤ ውፍረት ደግሞ ለብዙ በሽታዎች በር ይከፍታል። ስለዚህ ምግብ ስንመገብ ሳህኑ ግማሽ ያህል አትክልትና ፍራፍሬ እንዲሆን ማድረግ ጥሩ ነው። ጥራጥሬ፣ ስጋ እና ወተት ተዋጽኦዎችም በመጠኑ መጠቀም ያስፈልጋል።

ሦስተኛው ነገር እንቅስቃሴ ነው። ሰውነታችን እንዲሠራ ተደርጎ የተፈጠረ ነው። ስለዚህ ሁልጊዜ ተቀምጦ ወይም ተኝቶ መዋል የለብንም። በየቀኑ ቢያንስ ለሠላሳ ደቂቃ ያህል መራመድ፣ መሮጥ፣ ገመድ መዝለል ወይም ስፖርት መሥራት ያስፈልጋል። እንቅስቃሴ ማድረግ ልብን ያጠነክራል፣ ጭንቀትን ይቀንሳል እንዲሁም እንቅልፍን ያሻሽላል።

አራተኛው ነገር እረፍት ነው። ሰውነታችን ሲደክም ማረፍ አለበት። ሌሊት ቢያንስ ስምንት ሰዓት መተኛት ያስፈልጋል። ስልክ እና ቴሌቪዥን ከመጠን በላይ ማየት እንቅልፍን ይረብሻል። ስለዚህ ከመተኛታችን በፊት ስልክን ማራቅ ጥሩ ልማድ ነው። ጤናማ ሰውነት ያለው ሰው ጠንካራ ነው፣ ደስተኛ ነው፣ ሥራውንም በደንብ መሥራት ይችላል።

ውድ ወዳጆቻችን፤ ጤና ማለት ሀብት ነው። ሀብት ደግሞ ሲጠፋ ተመልሶ ለማግኘት ከባድ ነው። ስለዚህ ጤናችንን ዛሬ ከጠበቅን ነገ ሐኪም ቤት ከመሄድ እንድንድ

ՀԱՅԿԱԶ

«ՀԱՅԿԱԿԱՆ ՀԱՐՑԵՐԸ ՄԵԶ ՀԱՄԱՐ ՉԵՆ ԳՈՅԱՑՆԵԼ»

ՀԱՅԿԱԶԻ ՀԱՐՑԱԶՐՈՒՅՑԸ ՊԱՏԱՍԽԱՆՈՒՄ Է ՀԱՅԿԱԿԱՆ ՀԱՐՑԵՐԻՆ



ՀՀ ԱԶԳԱՅԻՆ ԺՈՂՈՎԻ ԱՐՏԱՀԵՐԹ ԿԱՆՈՆԱԴՐԱԿԱՆ ՀԱՆՁՆԱԺՈՂՈՎԻ ՆԱԽԱԳԱՀ ՀՐԱՆՏ ՆԱԶԱՐԵԹՅԱՆԸ ՀԱՅԿԱԶԻ ՀԱՐՑԵՐԻՆ ՊԱՏԱՍԽԱՆԵԼ Է ՀԱՅԿԱԿԱՆ ՀԱՄԱՅՆՔՆԵՐԻ ՄԱՍԻՆ ԵՎ ՀԱՅԿԱԿԱՆ ՀԱՄԱՅՆՔՆԵՐԻ ՄԱՍՆԱԿՑՈՒԹՅԱՄԲ ՀԱՅԿԱԿԱՆ ՊԵՏՈՒԹՅԱՆ ՔԱՂԱՔԱԿԱՆՈՒԹՅԱՆ ՄԱՍԻՆ:

ՀԱՐՑԱԶՐՈՒՅՑԸ ՎԱՐՎԵԼ Է ՀՀ ԱԶԳԱՅԻՆ ԺՈՂՈՎԻ ԱՐՏԱՀԵՐԹ ՀԱՆՁՆԱԺՈՂՈՎԻ ՆԱԽԱԳԱՀ ՀՐԱՆՏ ՆԱԶԱՐԵԹՅԱՆ ՀԵՏ ՀԱՅԿԱԿԱՆ ՀԱՄԱՅՆՔՆԵՐԻ ՄԱՍՆԱԿՑՈՒԹՅԱՄԲ ՀԱՅԿԱԿԱՆ ՊԵՏՈՒԹՅԱՆ ՔԱՂԱՔԱԿԱՆՈՒԹՅԱՆ ՄԱՍԻՆ:

Հ.- Ինչպե՞ս կգնահատեք Հայկական համայնքների հետ աշխատանքի ներկա վիճակը:

- Ես կարծում եմ, որ Հայաստանի իշխանությունները, ինչպես նաև հասարակությունը, ավելի ու ավելի են գիտակցում Հայկական համայնքների դերը Հայաստանի զարգացման գործում: Ես կարծում եմ, որ Հայկական համայնքների հետ աշխատանքը ներկայումս ավելի ակտիվ է, քան երբևէ: Ես կարծում եմ, որ մենք ունենք ավելի լավ հնարավորություններ, քան երբևէ, Հայկական համայնքների հետ աշխատելու համար: Ես կարծում եմ, որ մենք ունենք ավելի լավ հնարավորություններ, քան երբևէ, Հայկական համայնքների հետ աշխատելու համար: Ես կարծում եմ, որ մենք ունենք ավելի լավ հնարավորություններ, քան երբևէ, Հայկական համայնքների հետ աշխատելու համար:

Հ.- Ինչպե՞ս կգնահատեք Հայկական համայնքների հետ աշխատանքի ներկա վիճակը:

- Ես կարծում եմ, որ Հայաստանի իշխանությունները, ինչպես նաև հասարակությունը, ավելի ու ավելի են գիտակցում Հայկական համայնքների դերը Հայաստանի զարգացման գործում: Ես կարծում եմ, որ Հայկական համայնքների հետ աշխատանքը ներկայումս ավելի ակտիվ է, քան երբևէ: Ես կարծում եմ, որ մենք ունենք ավելի լավ հնարավորություններ, քան երբևէ, Հայկական համայնքների հետ աշխատելու համար: Ես կարծում եմ, որ մենք ունենք ավելի լավ հնարավորություններ, քան երբևէ, Հայկական համայնքների հետ աշխատելու համար:

Հ.- Ինչպե՞ս կգնահատեք Հայկական համայնքների հետ աշխատանքի ներկա վիճակը:

- Ես կարծում եմ, որ Հայաստանի իշխանությունները, ինչպես նաև հասարակությունը, ավելի ու ավելի են գիտակցում Հայկական համայնքների դերը Հայաստանի զարգացման գործում: Ես կարծում եմ, որ Հայկական համայնքների հետ աշխատանքը ներկայումս ավելի ակտիվ է, քան երբևէ: Ես կարծում եմ, որ մենք ունենք ավելի լավ հնարավորություններ, քան երբևէ, Հայկական համայնքների հետ աշխատելու համար: Ես կարծում եմ, որ մենք ունենք ավելի լավ հնարավորություններ, քան երբևէ, Հայկական համայնքների հետ աշխատելու համար:

Հ.- Ինչպե՞ս կգնահատեք Հայկական համայնքների հետ աշխատանքի ներկա վիճակը:

- Ես կարծում եմ, որ Հայաստանի իշխանությունները, ինչպես նաև հասարակությունը, ավելի ու ավելի են գիտակցում Հայկական համայնքների դերը Հայաստանի զարգացման գործում: Ես կարծում եմ, որ Հայկական համայնքների հետ աշխատանքը ներկայումս ավելի ակտիվ է, քան երբևէ: Ես կարծում եմ, որ մենք ունենք ավելի լավ հնարավորություններ, քան երբևէ, Հայկական համայնքների հետ աշխատելու համար: Ես կարծում եմ, որ մենք ունենք ավելի լավ հնարավորություններ, քան երբևէ, Հայկական համայնքների հետ աշխատելու համար:



ደቅርታ ደራሽ ወንዝ ያሻግራል

በጋዜጣው ሪፖርተር

ያለፈው ዓመት በርካታ መልካም መልካም ነገሮች የሰራንበት ነው። አይቻልም፣ አይሰራም ብለን የምንፈራቸው፣ ያልደፍርናቸው የተሰሩበት ዓመት፤ ብዙ ብዙ የልፋት ውጤቶች አግኝተን የተደሰትንበት ታሪካዊ ጊዜ ነበር። እናቶቻችን መሀረባቸውን ፈትተው፣ አባቶቻችን ከቦርሳቸው ዘግነው፣ ተማሪዎች የትራንስፖርታቸውን አጠራቅመው ሌላውም ካለው ቀንሶ ቦንድ ሲገዙ፣ ስጦታ ሲያበረክቱ የቆዩበትን የታላቁን ህዳሴ ግድብ የመጀመሪያ ዙር የውሀ ሙሌት በስኬት የተጠናቀቀበት ዓመት ነበር። በሸገርን ማስዋብ ፕሮጀክቶች አይነኬ ቤተመንግስቶቻችን ተውበውና አምረው የአይን ማረፊያ ሆነው ያየንበት፣ አስደናቂው የወንዝ ዳርና የእንጦጦ ፓርክ ፕሮጀክቶችን ለማመንም በሚከብድ መልኩ ተሰርተው እነሆ ለሀገር የተባሉበት ነበር። ሀገራችን የነበረች ድሮም የምናውቃት ሳይሆን አዲስ ሀገርና ከተማ እስክትመስለን ድረስ አስደማሚ ስራ የተሰራበት ዓመት ነው። በፖለቲካው፣ በማህበራዊና በኢኮኖሚ ዘርፉ አስደናቂ ክስተቶች ያየንበት ተደንቀንና ተደስተን «ለካስ ይሄም አለ» ብለን የተደመምንበት ዓመት ጭምር ነው። ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን በተለያየ መልኩ በዓለም አደባባይ ስማችን ከፍ ያለበት ታሪክ ሰሪነታችንን ዳግም ያስመሰከርንበት ጊዜ ነበር።

ደግሞም የዓለም አንዱ አካል ነንና አለምን ያንቀጠቀጠው፣ ምሁራንን ያርበደበደው የህክምና ጠበብቶችንና ሳይንቲስቶችን የፈተነውን የኮቪድ 19 ወረርሽኝ ያስተናገድንበት ዛሬም ድረስ ከችግሩ ጋር የቆየንበት ነው። በዚህም በህመም የተሰቃዮ ወገኖቻችንን ህይወት ለማትረፍ የጤና ባለሙያው ግብግብ የገጠመበት፣ በህይወት ያጣናቸውን አዝነን የሸኘንበት ዓመት ነበር ማለት ይቻላል። ኢትዮጵያውያን ከርሞም የመረዳዳት ባህል ያላቸው፣ ላጣ ለነጣ መስጠት ድሮም የነበረ አሁንም የቀጠለው መተሳሰባችን እስከዛሬው ድረስ ቆይቷል።

ያም ሆኖ ግን ብዙ ምስቅልቅል የህይወት መንገዶችን ለመጓዝ የተገደድንበትም ነበር። ተማሪ ከትምህርቱ ተለይቶ መምህራኑ ከመደበኛ ስራቸው ሌላው በተመሳሳይ ቁጭ በቤት የታወጀበት እንደነበር እናስታውሳለን። ህጻን አዋቂው የተማረ ያልተማረ ደሀ ሀብታም ሳይባል አንድ አይነት ቋንቋ የተነጋገርንበት ክስተት። እንኳንስ እንደ እኛ ያሉትን ደሀ ሀገራት ቀርቶ በዓለም የኢኮኖሚ ኮርቻ ላይ የተቀመጡትን ጭምር የፈተነ እንደነበር መጥቀስ የግድ ይላል። አለምን በኢኮኖሚው፣ በፖለቲካው፣ በማህበራዊ ጉዳይ ሳይሆን በሚያደርሰው የጤና ጉዳት በሚሰጠው የመከላከል አገልግሎት በሚደረገው የጥንቃቄ ስራዎች አንድ ቋንቋ ያነጋገረ ነበር።

ከዚሁ ጎን ለጎን ደግሞ በጣም አሳዛኝ ከኢትዮጵያውያን የማይጠበቅ፣ በኢትዮጵያውያን ይደረጋል ተብሎ የማይታሰብ አሰቃቂ ክስተቶችንም ያስተናገድንበት ነበር። ብዙዎች ህይወታቸውን ያጡበት፣ ሀብት ንብረታቸው የወደመበት፣ ከመኖሪያ ቀያቸው የተፈናቀሉበት መጥፎ ጊዜያትን ማሳለፋችንን እናስታውሳለን። ሀገራችንን የብዙ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ሀገር የተለያየ ቋንቋ ተናገሪዎች ያሉበት፣ የተለያዩ ባህል ባለቤቶች፣ የእምነት ልዩነትን ያለ ልዩነት በፍቅር በመተሳሰብና በመቻቻል የሚያከብር ህዝብ ባለቤት ናት። ይሁን እንጂ ባለፈው ዓመት ፍጹም ሊታመን በማይችል መልኩ በአብሮነት ተጋብቶ፣ ተዋልዶ፣ ተዛምዶ የሚኖርን ህዝብ ለመለያት፤ አንዱ በሌላው ላይ እንዲዘምት ተደርጎ የደም መፋሰስ የተስተዋለበት እንደነበር አንዘነጋውም። ታዋቂ፣ ለሀገር ለወገን አለሁ ባይ ወገኖቻችንን በግፍ ያጣንበት ዓመት ነበር። ለብዙዎች እንጀራ የሆኑ ሀብቶች በግፍ የወደሙበት ብዙ ትርምስምስ ሀሳቦች ሲነዙ የከረሙበት እና ከዚሁ ጋር ተያይዘም ማየት የማይገባንን ያየንበት ዓመት ነበር። የሴራ ፖለቲካን የተረዳንበት፤ ሀገር ለማፍረስ ዜጋን ለመበተን የሚደረጉ ሩጫዎች የከሸፉበት ጊዜም ነበር።

እንግዲህ በእነዚህ ሂደቶች ውስጥ አጥፊ አለ፤ በሰዎች ደም ስልጣን ለማግኘት፣ እውቅና ለማትረፍ የሚሮጠው ብዙ ነው። አንዱን ዘር በሌላው፤ አንዱን ሀይማኖት በአንዱ ላይ በማነሳሳት ከዚህም የከፋ ችግር እንዲከሰት የሰሩ፣ ያሰሩ፣ ሲመሩ የነበሩ፣ ያስተባበሩ፣ በገንዘብና በእውቀት የደገፉ አባሪ ተባባሪ ጭምር ተያይዘው ወደ ማረሚያ የተወረወሩትም በዚሁ ዓመት ነው። ህግ ከማንም በላይ ነውና የህግ የበላይነት እንዲከበር ከህዝቡ ሲሰማ የነበረው ውትወታም ውጤት የታየበት ነበር። ከምላ ጎደል ዛሬ አንጻራዊ ሰላም ሰፍኗል። የህዝብ ስጋት ቀንሷል።

በዚህ ሂደት መካከል በዳይና ተበዳይ ተፈጥሯል። ጥላቻ ሰፍኗል። ቂም ያረገዙ ብዙ አይደሉም ለማለት አይቻልም። ቂም ግን ጥቅም የለውም፣ የጠፋ ህይወት አይመልስም፤ የወደመ ሀብትን አይካስም፤ እና አሁን የሚያስፈልገው ይቅርታ ብቻ ነው። በእውቅትም ሆነ ያለ እውቀት ለተሰራው በይቅርታ መተላለፍ ጊዜው ይጠይቃል። አናካሾቻችንን ካልነቃንባቸው በይቅርታ ተማምረን መረዳዳት ካልቻልን ነገ ከዚህ የበለጠ ችግር እንደማይገጥመን ዋስትና የለንም። እናም ተፈጥሮ የነበረውን ለታሪክ ትቶ በአዲሱ ዓመት አዲስ አቅጣጫ ማየት ያስፈልጋል። በይቅርታ ቀን ይቅርታን አጉልቶ መዘመር ላለፈው ሳይሆን ወደፊት ሌላ አስከፊ ነገር እንዳይገጥመን ይረዳል። በይቅርታ ደራሽ ወንዝን በጥበብ እንሻገራለን።

ወጋ ወጋ

ቅዝምዝምን ማሳለፍ ....!

በጋዜጣው ሪፖርተር

አንድ አስቸጋሪ ጉዳይ ሲያጋጥመኝ ምክር የሚሰጠኝ አንድ ጓደኛ አለኝ፤ ጓደኛዬ አሁን ድረስ የሆነ ነገር ሲሰማ እንዴት ነው ይሄ ጉዳይ? ሲል ይጠይቃል። እኔም ያለውን ሁሉ ሳልደብቅ አጫውተዋለሁ፤ መቼም ምክሩ እንደ እድሜው አይደለም ግራ ቀኝ የፊት የኋላ አይቶ ለዚህኛው ጉዳይ ይህንን ብታደርጊ ጥሩ መፍትሄ ነው ሲል ምክሩን ይለግሳል። በዛ ላይ ደግሞ ለሰዎች ቅን አሳቢ እድገት ተመኚ በመሆኑ የተሳሳተ ነገር እንኳን የተናገረ ቢመስለኝ በእኔ ልብ ውስጥ እሱን ለመቀየም የሚሆን ቦታ የለም። እና እንደለመደውና እንደለመድኩት ቆይተን ስንገናኝ ስለ ቤተሰብ ፣ አካባቢያችንን፣ ስለ ዘመድ አዝማድ፣ የስራ ሁኔታ ሁሉን እያነሳን እንጨዋወታለን። አንዳንዴ "ይሄን ጎንበስ ብለሽ" ... ይልና ፈገግ ይላል።

እውነት ነው አንዳንድ ጉዳይ ጎንበስ እያሉ ካልሆነ ማለፍ ይከብዳል። እንቧ ግንባሬን ለጥይት ማለቱ ትርፉ በተተኮሰው ጥይት መበሳሳት ብቻ በመሆኑ የሚሻለው ጎንበስ ብሎ ማሳለፉ ነው። ጎንበስ ብለን ያለፍናቸውም እንዲያ እንዳንሆን አድርገዋል።

አንዳንዱ የሚያሰበው በጭንቅላት ቀርቶ በዘሩ ይሆንና ከእሱ ውጪ ያሉ ወንድም እህቶቹን ሶስተ አራተኛ ዜጋ አደርጎ ይቆጥራል፤ አንዳንዱ ደግሞ ከዛም አለፍ ሳይል ይቀራል ብላችሁ ነው። እንጃ ብቻ እኔ እንደዛ አይነት ባዕድነት እየተሰማኝ ነው። የተለየ ፖለቲካዊ አስተሳሰብ አለው ወይም በእውቀት ይበልጠኛል አልያም እነእከሌን ይደግፋል ብሎ ሲያስብ ለአይጥ እንደሚያዘጋጀው ወጥመዱን ከወዲያ ወዲህ ያጠምዳል ።

አንዳንዱ ደግሞ የሚያሰራው አንድን የሀይማኖት ተከታይ ለመጥቀም እስኪመስል ድረስ ይሆናል። ወደላይ ካሉት ጋር ቅርበት አላቸው ያላቸውን ሰዎችማ ቢቃ ያለስራቸው ሲካቡ ፣ያለጀግንነታቸው ሲወደሱ ይከርማሉ። የሰንሰለቱ ማስገቢያ ግን በአንድ አጋጣሚ ብጥስ ሲል ያው እንዳየነው እንደለመድነው ብትንትኑ መውጣቱ የማይቀር ነው ። በዚህ መንገድ የተጓዙ ብዙ ነበሩ ፤ ግን አደጋውም እንቅፋቱም፤ ድንቅፍቅፉም ገጥሟቸዋል። አንዳንዶች ታዲያ ማሊያ ለመገልበጥ ልዩ ጥበበኞች ናቸውና አምነውም ይሁን ሳያምኑበት ማሊያቸውን ገልብጠው የሆነውን ሆነው ብቅ ይላሉ። አልሰሜ ቃር ቃር ሲለው... ።

ነገርን ነገር ያነሳዋል ሆነና ነው እንጂ መነሻዬ እንኳን ያቺዋ አሜሪካን የምንላት ሀገር ናት። የሰሞኑ ወሬዎች አሜሪካ ለኢትዮጵያ የምትሰጠውን እርዳታ ልትቀንሰ ፣ ልታግደ ነው የሚሉ ናቸው ። እርግጥ ሀገራችን ዓመታዊ በጀቷን ጭምር የምታሟላው ከውጪ ሀገራት በምታገኘው እርዳታና ብድር በመሆኑ እርዳታው ያስፈልገናል። እርዳታና ብድሩ ያስፈልገናል ብለን ግን ክብራችንን አናዋርድም፤ ለአመት ብድርና እርዳታ ብለን ዘላለማዊ ጥቅማችንን አሳልፈን አንሰጥም። በእርግጥ ታላቅ ፣ ሰጪ ይከበራል ፣ ይመሰገናል። ይሄ የሚሆነው ግን ክብር እስካልነካ ድረስ ነው። ስለምሰጥህ ተብሎ የሚረገጥ ዜጋ መቼም በኢትየጵያ ምድር አይኖርም፤ ኖሮም አያውቅም።

አሜሪካ ምንም ብትል የከፉ ቀን ባለውለታችን በመሆኗ እናከብራታለን። ወደፊትም አብረን የምንጓዝ ነን። ታዲያ ሰጥቶ የመቀበል ፤ የሁለትዮሽ ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት እንጂ ሌላ ሊሆን አይችልም። ደግሞም አይሆንም ። ደሀ እኮ ቆራጥ ነው። ምንም ባይኖረውም ያለውን ይዞ ለነገው ይሰራል። ይሄን ሲያደርግ ከጎረቤት ከዘመድ አዝማዱ እየተጣላ ሳይሆን የሚሰነዘረውን ሁሉ በትዕግስት ጎንበስ ብሎ እያሳለፈ ነው። አሁንም ከወደአሜሪካ የሚታየውን ጎንበስ ብሎ በጥበባዊ ዲፕሎማሲ ማለፍ ሳይበጅን አይቀርም። ለግብጽ እረዳለሁ እኔ ያልኩት ካልተፈጸመ ብሎ ጉልበቱን ሊያሳየን ለሞከረ መልሳችን ያው ነው።

ከእርሶ ለእርስዎ

የጎርፍ አደጋ የበዛው ለምን ይመስልሀል?

በላይ ዋሴ (ከጎንደር)

መልስ- ከተፈጥሮ ጋር በመታረቃችን

አከራዬ ሰሞኑን ፀባያቸው ተቀይሯል ለምን እንደሆነ አላወቅኩም እስኪ ገምት?

አየለ ዘለቀ (ከሳር ቤት)

መልስ - የጳጉሜን የቤት ኪራይ ስለማትከፍላቸው

በዚህ ዓመት ፈተና የሆነብህ ጉዳይ ምን ነበር?

ከበደ (ከገርጂ መብራት)

መልስ- ኮቪድ 19

የትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጡ አዲሶቹ ሜትር ታክሲዎች ህዝቡን ለዝርፊያ እያጋለጡት ነው አሉ እውነት ነው?

ሰመረዲን መሀመድ (ከመርካቶ)

መልስ - አሉባልታ አትውደድ፤ በመረጃ አስደግፍ

በሚቀጥለው ዓመት ዕቅዴ ልጅ መውለድ ነው፤ ነገር ግን እስካሁን አላገባሁም፡፡ እቅዴ እንዲሳካ ምን አድርጊ ትለኛለህ?

ባንቺይሁን ንጋቱ (ከቦረና)

መልስ - ላም ባልዋለበት ኩበት ለቀማ

አባቴና እናቴ በኔ ምክንያት ተጣልተዋል፤ እኔ ደግሞ ምክንያት መሆኔ አሳስቦኛል እስኪ እንዲታረቁ አንድ መላ ንገረኝ

ግርማቸው ሰመረ (ከግንፍሌ)

መልስ - ጳጉሜ አንድ የይቅርታ ቀን መሆኑን አልሰሙ ይሆን

ሰሞኑን ምግብ አልጠግብ ብያለሁ፤ ምን ላድርግ?

ወንድሜነህ ንጉሴ (ከአየር ጤና)

መልስ - አምስቱን የጳጉሜ ቀናት በዶም በጸሎት አሳልፍ

አዲስ ዓመት በአዲስ መንፈስ መቀበል እፈልጋለሁ፤ በምን ብጀምር ጥሩ ነው?

ሰርካለም ሙሳት (ከ4 ኪሎ)

መልስ - በይቅርታ እና በልግስና

ድንቃ ድንቅ

ሳሙኤል ዘሪሁን

- የአይርላንዱ ጠቅላይሚኒስትር ሊዮ ቫራድካር ከኮሮና መከሰት በኋላ የህክምና አገልግሎት ለመስጠት ዳግም የህክምና አገልግሎት ምዝገባ በማድረግ በሳምንት አንድ ቀን በፈረቃ ለመስራት ተነሳሽነታቸውን አስመስክረዋል።
- ቫራድካር ወደ ፖለቲካው አለም ከመግባታቸውና ከህክምናው መዝገብ እአአ በ2013 ከመሰረዛቸው በፊት ለ 7 አመታት የህክምናው ዶክተር በመሆን አገልግለዋል ።
- የ2019 ሚስ ኢንግላንድ ባሃርሻ ሙከርጂ የቁንጅና የክብር ዘውዷን አስቀምጣ ወደ ቀደመው የዶክተርነት ስራዋ ተመልሳለች። ይሄ የኮሮና ቫይረስን ለመመከት የተደረገ ውሳኔ ነው።
- በአሁን የኮሮና ወረርሽ ወቅት በህንድ መንታ ልጆች የወለዱት ባለትዳሮች የልጆቻቸውን ስም «ኮሮና» እና «ኮቪድ» ብለው መሰየማቸው አነጋጋሪ ሆኗል።
- የወንዱ ልጅ ስም «ኮቪድ» ሲባል የሴቷ ደግሞ« ኮሮና» ተብለዋል።
- በዚሁ በህንድ ኡታር ፕራዴሽ ግዛት ለተወለዱ መንትያ ልጆች «ካራንታይን» እና«ሳኒታይዘር» ብለው ስም ያወጡ ወላጆችም አሉ።
- ማህበራዊ እርቀትን በመጠበቅ የኮሮና ቫይረስን መከላከል ይቻላል የሚለውን የህክምና ባለሙያዎች ምክር የሰሙ በሩሲያ ስቬርድ ሎቭስክ ግዛት የሚገኙ የአምስት ቤተሰብ አባላት ከሚኖሩበት መንደር እሩቅ ተጉዘው ጫካ ገብተዋል።
- ሶሰት ልጆቹን እና ባለቤቱን ይዞ ወደ ጫካ የገባው የ 33 አመቱ አባወራ ቤታችንን ጥለን ወደ ጫካ የገባነው በኮሮና ቫይረስ እንዳንጠቃ ፣ ልጆቼን እና ባለቤትን እንዳላጣ ነው ሲል ለፖሊስ ተናግሯል።
- በጫካውም ለቀናቶች እንደቆዩ እና የቫይረሱ ስርጭት ጋብ ሲል ወደ ቤታቸው ለመመለስ አስበው እንደወጡም አባወራው ለፖሊስ አስታውቋል።
- በጀርመን የበርሊን ቅርንጫፍ ከንቲባ ስቴፈን ሮን ዴዝል በኮሮና ቫይረስ ከተያዙ ሰዎች ጋር ሆን ብለው ግንኙነት በማድረግ በቫይረሱ ተይዘዋል።
- ከንቲባው ይህንንም ያደረጉት በሽታ የመቋቋም አቅማቸውን ለማወቅ እና ሌሎች በበሽታው ምክንያት ከቢታቸው ሲቀሩ እርሳቸው በሽታውን አሸንፈው ከስራ ገበታቸው ላይ መገኘት ይችሉ እንደሆነ ለማወቅ መሆኑን ተናግረዋል።
- በትውልድ ግሪካዊ የሆነው ፓፓ ዲማትሩ የተባለው ተማሪ ከ ግሪክ ወደ ስኮትላንድ አቅንቶ በስኮትላንድ አበርዲን ዩኒቨርስቲ ትምህርቱን ይከታተል ነበር። የኮሮና ቫይረስ መከሰቱን ተከትሎ የሚማርበት ዩኒቨርስቲ ላልተወሰነ ግዜ በመዘጋቱ እና በረራ በመቋረጡ ምክንያት ወደ መኖሪያ ሃገሩ ግሪክ ለመመለስ 48 ቀናትን በብስክሌት ተጉዟል
- በጉዞው እንግሊዝ፣ ኔዘርላንድ፣ጀርመን፣ኦስትሪያ እና ጣሊያንን አቋርጧል።
- በህንድ ነዋሪነቱን ያደረገው አስላም የተባለ ግለሰብ በኮሮና ቫይረስ የተያዙ ሰዎችን እጃቸውን በመሳም ብቻ እፈውሳለሁ ቢልም እራሱ በኮሮና ቫይረስ መሞቱ ተሰምቷል ።

ምንጭ፣ ሴክስፕረስ ኒውስ ሰርቪስ እና ኦዲቲ ሴንትራል ናቸው

የዘመን ኪነ ጥበብ

አገራዊ ጉዳዮችን የዘነጉ ፊልሞቻችን

ተገኝ ብሩ

ኪነ ጥበብ አገራዊ ገፅታን በመገንባት፣ ባህልን በማጎልበትና የማህበረሰቡ ትስስር በማጠናከር በኩል የሚጫወተው ሚና ከፍተኛ ነው። ይህንን ዘርፍ በወጉ ከተገለገሉበት በቀላሉ ማህበረሰባዊ የአስተሳሰብ ለውጥ ለማምጣትና ለበዙ ልማታዊና አገራዊ ጉዳዮች ማነልበቻነት ይጠቅማል። በማህበረሰባዊ ሁለንተናዊ ለውጥ የላቀ ደረጃ ላይ የሚገኙ አገራት ኪነ ጥበብን ለለውጣቸው ማፍጠኛነት እንደ እርሾ ተገልግለውበታል።

ኪነ ጥበብ ማስተሳሰሪያ ገመድ ነው። ከኪነ ጥበብ ዘርፎች አንዱ የሆነው ፊልም የማህበረሰቡን ልዩ ልዩ መልኮች አጎልቶ በማሳየት የጎላ ድርሻ አለው። የአንድን አገር ማህበራዊ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች በፊልሞቻቸው ለሌላው አለም ከማሳየትና ከማስተዋወቅ ባለፈ ሀገራዊ ፍቅርን በማሳደግ የህዝባቸውን የእርስ በእርስ ትብብር ያጎለብታሉ ።

የማይገናኝና የተራራቀ ነገር እንኳን ወደ አንድ ማቅረብ የሚቻልበት የሀሳብ ልዕልናን ማስረፅ ሰብዓዊነትን ማነፅ የሚያስችለው ኪነ ጥበብ በተለይ ፊልም እኛ አገር ላይ የሚጠበቅበትን ያህል ለውጥ መፍጠር እንዳልቻለ ይነገራል። ኢትዮጵያዊያን የእርስ በእርስ ትስስራችን የጠነከረ፣ አብሮነታችን እንዳይበጠስ ሆኖ የተጋመደ፣ ከምንለያይበት ይልቅ የምንጋራቸው ነገሮች የበዙ፣ ስነ ልቦናዊ ጥምረታችን በጉልህ የሚታይ ድንቅ ህዝቦች ነን።

ይህ አብሮነታችን ጎልቶ የምንኖረው አንድነታችን ገዝፎ በኪነ ጥበቡ በተለይም በፊልሞቻችን መታየትና የራሱ ተፅዕኖ መፍጠር ያልቻለበት ምክንያት ምን ይሆን? ለምን ፊልም ሰሪዎቻችን አንድነታችንን ለማጠንከር የእርስ በእርስ ትስስራችንን ለማጠንከር በሚያስችሉ ጉዳዮች ላይ ትኩረት ተሰጥቶ አይሰሩም? በሚለው ዙሪያ ለመወያየት ለዛሬው የኪነ ጥበብ አምድ ላይ ትኩረት አድርገናል።

ፊልሞች ማህበራዊ ትስስርን እና አብሮነትን በማጠንከር ለሁለንተናዊ ለውጥ ታላቅ ጠቀሜታ እንዳላቸው የማይካድ ሀቅ ነው። ነገር ግን እነዚህ አብሮነታችን ጎልቶ እንዲታይ የሚያደርጉ የኪነ ጥበብ ስራዎች በዋናነት ፊልሞች የሚገባው ያህል እንዳልተሰሩ ባለሙያዎች ይናገራሉ። እንደ ፊልም ባለሙያዎቹ ፊልሞቻችን አገራዊ ጉዳይ ላይ የማያተኩሩበት ምክንያት የተለያየ ቢሆንም በይዘት ደረጃ ግን ሀገራዊ ጉዳዮች የሚያነሱ የእርስ በእርስ ግንኙነትን የሚያጠነክሩ ፊልሞች የሚገባውን ያህል እንዳልተሰሩ ተመሳሳይ የሆነ አስተያየት ይሰጣሉ።

ረዲ በረካ (ሴት ልጅ) የፊልም ስራ ባለሙያ ነው። 10 በሚሆኑ ፊልሞች ላይ በድርሰትና በአዘጋጅት እንዲሁም “እጅ ወደ ላይ” የተሰኘ ቲያትር በድርሰትና በአዘጋጅነት ተሳትፎ አድርጓል። ከፊልሞቹ 50 ሎሚ፣ ሱማሌው ቫንዳም፣ የህዝብ ነኝ ሰማያዊ ፈገግታ፣ ወራጅ አለ፣ የትነበርሽ፣ በ17 መድፌ ከፊልሞቹ መሀል ተጠቃሾቹ ናቸው።

አገራዊ አንድነትን ለመገንባትና የእርስ በእርስ ትስስርን ለማጠንከር ፊልሞች የጎላ ሚና እንዳላቸው እምነቱ ነው። በዘርፉ በቂ የሆነ ስራ ቢሰራ የተሻለ ውጤት ማስመዝገብ እንደሚቻል ይገልፃል። በተለይ አሁን ያለንበትን ሁኔታ ወደተሻለ ገፅታ ለመቀየርና መግባባትን ለመፍጠር ፊልሞችን ትልቅ መሳሪያ ማድረግ እንደሚቻል ይናገራል።

ይዘታቸው ሀገራዊ የሆኑ ፊልሞች የሚጠበቀውን ያህል ባይሆንም የሉም በሚባል ደረጃ ላይ እንዳልሆኑ ይጠቅሳል። በተለያዩ ባለሙያዎች ትልልቅ ተፅዕኖን የፈጠሩ በርካታ ሀገራዊ ይዘት ያላቸው ፊልሞች መሰራታቸውን ያነሳል። በእርግጥ ማህበራዊ ጥምረትና አብሮነት ላይ የተሰሩ ስራዎች ቁጥራቸው አነስተኛ መሆኑን ያምናል።

ፊልም ሰሪው የማህበረሰቡን አብሮ የመኖር መልካም እሴት የሚያጎለብቱ ሀገራዊ ፍቅርን ከፍ የሚያደርጉ

> ዛሬ ላይ የዓለም አገራት የፊልም ዘርፉ ወሳኝ መስክ መሆኑን ተረድተውና ልዩ ትኩረት ሰጥተው ይሰሩበታል። ለዘርፉ የሚፈልገውን ድጋፍ አድርገው አላማቸውን ያሳካሉ። የኢትዮጵያ ፊልሞችን ይዘትንም አገራዊ ገፅታ በማላበስ የተሻለ አገራዊ ስሜትና አንድነት በማጠናከር ትልቅ አቅም መፍጠር የሚችል ማድረግ ይገባል

ሀገራዊ ፊልሞች መስራት እንዲያስችለው ለዘርፉ ልዩ ትኩረት መስጠት ያስፈልጋል። ፊልም ሰሪው የፈለገውን ይዘት በተለይም አገራዊ ጉዳይ ላይ ያተኮሩ ፊልሞች መስራት እንዳይችል ያደረገውን ምክንያት ይዘረዝራል።

የፊልም ባለሙያው ክህሎትና እውቀት ችግር፣ ስለ አገሩ ያለው በቂ የሆነ እውቀት አለመኖር፣ የፊልም መስሪያ በጀትና ግብዓት እጥረትና ከዚህ በፊት የነበሩት የፊልም ግምገማ በዋናነት ይጠቅሳል። በእርግጥ ፊልም ሰሪው በጉዳዩ ላይ ትኩረት አድርጎ በትብብር ያለመስራት ውስንነት እንዳለም ይጠቁማል።

አገራዊ ፊልም የሚያስብሉ የፊልም ይዘቶች በአብዛኛው ፊልም ሰሪና ማህበረሰቡ በተሳሳተ መንገድ እንደሚወሰድ የሚገልፀው ደራሲና አዘጋጅ ረዲ በረካ ሀገራዊ ፊልም ማለት የተለያዩ አካባቢዎች ዘዬ አላብሶ መስራትና ወደ ገጠራማ አካባቢዎች ወጣ ብሎ መስራት የሚመስለው ብዙ የተሳሳተ አሳቤ እንዳለ ያስረዳል።

በእርግጥ የተለያዩ ታሪኮችና መቼቶች ማሳየትም አገራዊ የሆነ ገፅታን ማጉላት ነው የሚለው ባለሙያው ነገር ግን ከዚህ ለየት ባለ መልኩ መታሰብ እንዳለበትና ሀገር ተኮር የሆኑ ፊልሞች አገራዊ ጉዳይ አንስተው የማህበረሰቡን የእርስ በርስ ትስስር የሚያጠነክሩና አገራዊ ፍቅር የሚያሳድጉ መሆን እንደሚገባቸው ይመክራል።

ተዋናይ ግሩም ኤርሚያስ በአማርኛ ፊልሞች የትወና ብቃት አድናቆትን ያተረፈ አርቲስት ነው። ፊልሞች የእርስ በርስ ግንኙነትን በማጠናከርና ሀገር በመገንባት ያላቸው ሚና ከፍተኛ መሆኑን ያስረዳል። በተለይ ከአገር አልፎ በውጭ አገራት ጭምር አገርን በማስተዋወቅ የአምባሳደርነት ሚና እንዳለው ያስረዳል። በተለይ አገራት የገፅታ ግንባታቸውን የህዝባቸውን ስነ ልቦናዊ ጥንካሬ ለመገንባትና በመልካም ነገሮች አሸናፊነትን በማስረፅ ትልቅ ሚና አላቸው።

የህዝቦችን ትስስር ለማጎልበትና የአገር ፍቅር ስሜት ከፍ ለማድረግ ትልቅ አቅም ያለው ፊልም መስራት ልዩ ትኩረት ያሻዋል። ትልቅ ተፅዕኖ መፍጠር የሚችልና አገራዊ ጉዳዮችን የሚዳስስ፣ አገርን የሚያስወድዱ የእርስ በርስ ግንኙነትን የሚያጠነክሩ ስራዎች በብዛትና በጥራት መስራት የሚገባ መሆኑን ያስረዳል።

የፊልም ባለሙያው በፊልም ሙያ ያለውን እውቀት ማጎልበትና የጋራ ትብብር፣ መንግስት ለዘርፉ የሚሰጠውን ድጋፍ ማጠናከርና በፊልም የሚገኘው ታላቅ አበርክቶን በመረዳት ትኩረት መስጠት ለፊልም ስራ እድገት ወሳኙ ጉዳይ ነው። በተለይም አገርን በአንድነት ለማስተሳሰርና የአገር ታላቅነት ለመዘገብ አዝናኝ በሆነ መልኩ የሚሰሩና የአገር ፍቅር ስሜትን የሚያሳድጉ ፊልሞች በብዛት መስራትና ማውጣት አገሪቱ አሁን ላለችበት ትኩሳት ለመውጣት የራሱ የሆነ አቅም አለው።

ፊልሞች አገር የማቅናትና ትውልድን የማነፅ ሚናቸው እጅግ በጣም የጎላ ነው። ሀገራት ማህበረሰብን ለሚፈልጉት በጎ አላማ ግብ ማነሳሳ በማድረግ ኪነ ጥበብን በተለይም ፊልምን በብዙ ይጠቀሙበታል። ይህ ዘርፍ ጉዳዮችን ማጣፈጫ፤ ለልዩ ልዩ መርህ ግብሮች ማዋጮ በመሆን ሁለገብነቱ የሰፋ ነው። እኛም እንደ አገር እያዝናኑ ቁም ነገር የሚያስጨብጡ ፊልሞችን በወጉ ከተጠቀምንባቸው ጉልህ ሀገራዊ ፋይዳ ሊያበረክቱ እንደሚችሉ አያጠራጥርም።

«የአገርን ጉዳይ ትኩረት ያደረጉ ፊልሞች አገሪቱ በሚያስፈልጋት መጠን አልተሰራም። እዚህ ላይ ትኩረት ተሰጥቶ መሰራት ይገባዋል» የሚል እስካሁን ከስድስት በላይ ፊልሞች ሰርቶ ለተመልካቾች ያቀረበው ዮሀንስ መራዊ ነው። በይዘታቸው አገራዊ ጉዳይ የሚያነሱ ፊልሞች በብዛት እንዳይሰሩ የፊልም ሰሪዎች ፍላጎት ማጣትና አቅም ዋነኛ ምክንያቶች መሆኑን የፊልም ባለሙያና ፕሮዲዩሰሩ ዮሀንስ መራዊ የራሱን አስተያየት ይሰጣል።

ዮሀንስ እንደሚለው ፊልሞች ሲሰሩ እንደ ጉዳያቸው ክብደት ትልልቅ በጀቶች ተመድበውላቸው ስለሆነ ፊልም ሰሪው ለመስራት የሚቀለው ጉዳይ ላይ ትኩረት ያደርጋል። በመሆኑም ለፊልም ስራው ነፃነት፣ የገቢ ምንጭ መጠንከርና ለሙያተኛው ምቹ ሁኔታ ሊፈጠርለት የሚገባ መሆኑ ያስረዳል።

ተመልካቹ ማየት የሚፈልገው የፊልም ይዘት ሌላኛው አገራዊ ይዘት ያላቸው ፊልሞች በፊልም ሰሪዎች ዘንድ እንዳይሞከር የሚያደርገው ሌላኛው ምክንያት መሆኑን ያስረዳል። ፊልም ሰሪው በቀላሉ ሰርቶ የሚያቀርበው ቀላል ይዘት ያለው የፊልም ጉዳይ ተመልካቹ የሚያይለት ከሆነ ለይዘቱ ትኩረት እንዲሰጥ ያደርገዋል።

ደራሲና ፕሮዲዩሰር ረዲ በረካ በዚህ አይስማማም። ተመልካቹ ጥሩ ፊልም ከተሰራለት ስራን አከብሮ የሚያይ መሆኑና በይዘት መረጣ ሳይሆን ጥራት ባለው መልኩ መሰራቱ ላይ ትኩረት እንደሚያደርግ ከዚህ በፊት አገራዊ ጉዳዮች ላይ የተሰሩ ፊልሞች በተመልካቹ ዘንድ ተወደው በስፋት ታይተው እንደነበር በመጥቀስ ያስረዳል።

የፊልሞች ዋነኛ አላማ አገራዊ ሁለንተናዊ ለውጥ በተሻለ መልክ መገንባት የእርስ በርስ ትስስር ማጠንከርና ህዝብን ማስተማር መሆን የሚገባው መሆኑን የሚገልፀው ተዋናይ ግሩም ኤርሚያስ የፊልም ሰሪዎችም ሆነ የመስኩ ባለሙያዎች ትኩረት ጠንካራ የሆነ አገራዊ ጉዳዮችን በማንሳት ለህዝብ ማቅረብና ማስተማር የሚገባቸው መሆኑን ያስረዳል። የባለሙያዎቹ የጋራ ስራ እንደሚጠይቅን ትልልቅ ስራዎች ሲሰሩ አብሮ ለተሻለ ውጤት እንዲበቁ መትጋት አስፈላጊ መሆኑን ይናገራል።

ዛሬ ላይ የዓለም አገራት የፊልም ዘርፉ ወሳኝ መስክ መሆኑን ተረድተውና ልዩ ትኩረት ሰጥተው ይሰሩበታል። ለዘርፉ የሚፈልገውን ድጋፍ አድርገው አላማቸውን ያሳካሉ። የኢትዮጵያ ፊልሞች ይዘትንም አገራዊ ገፅታ በማላበስ የተሻለ አገራዊ ስሜትና አንድነት በማጠናከር ትልቅ አቅም መፍጠር የሚችል ማድረግ ይገባል ሲሉ ባለሙያዎቹ ይመክራሉ።

ፊልሞች እንደ አገርም የፊልም ጠቀሜታ በሚገባ ተረድተን ለምንፈልገው አገራዊ ጠቀሜታ በሚውልበትና ለአገር ሁለንተናዊ ለውጥ የራሱን አዎንታዊ ተፅዕኖ መፍጠር የሚችልበት ሁኔታ ሊመቻች እንደሚገባ ባለሙያዎቹ ይናገራሉ።

በፊልም ዘርፍ በዓለም ላይ ትልቅ ደረጃ መድረስ የቻሉ አገራት ተሞክሮ ለሌላው ገፅታቸውን በማሳየትና ማንነታቸውን በማጉላት ላይ ትኩረት በማድረጋቸው መሆኑን የሚያስረዳው ዳራሲና አዘጋጅ ረዲ በረካ እራሳቸንን ሆነን በባህልና ወግን በጠበቀና አገራዊ ጉዳዮችን የዳሰሱ ጠንካራ ስራዎች በመስራት ለህዝቡ ማቅረብ ይገባል በማለት የራሱን አስተያየት ሰጥቷል።

አንድ ኢትዮጵያዎ ልጅ አገሩ ላይ ያሉ ከተሞችን ከማወቅ ይልቅ በፊልሞቻቸው ላይ ያሉ የውጭ አገር ከተሞችን አይቶ መለየት እንደሚችል ምሳሌ በመጥቀስ የሚያስረዳው ረዲ አገርን ማስተዋወቅና ማህበረሰባዊ እውቂያን ከፍ በማድረግ ሂደት የፊልም ሚና የላቀ መሆኑ ያስረዳል። በዚህም ፊልሞች ይዘታቸው ጠንካራና የማህበረሰቡን ትክክለኛ ማንነት በሚገልፅ መልኩ መሰራትና ለህብረተሰቡ መድረስ ይኖርባቸዋል በማለት ይገልፃል።

በባለሙያዎቹ የተነሳው ሌላኛው ጉዳይ በፊልም ጥበብ እንደ አገር ስልጠና የሚሰጡ ተቋማት አለመኖር ነው።በመሆኑም በዚህ ረገድ መሰራት ይገባል ይላሉ። ሙያውን ጠንቅቆ በሚያውቀው ሰው ሲሰራ በስራው የሚገኝ በጎ ነገር የሚበረክት መሆኑን ያነሳሉ። ደራሲውና ባለሙያው የሚወጣው ከማህበረሰቡ እነደመሆኑ መጠን ማህበረሰቡ አገሩን በሚገባ እንዲያውቅ ማድረግም ሌላው በአገር ደረጃ መሰራት የሚገባው ማህበረሰባዊ የቤት ስራ መሆኑን ይገልፃሉ።

የፊልም ባለሙያዎቹ አገርን በመገንባት ሂደት ውስጥ ህብረተሰቡን እያዝናኑ በማስተማር አገሩን እንዲወድ እና ስለ ማህበረሰቡ እንዲቆረቆር የሚያንፁ ይዘት ያላቸው ፊልሞች ማዘጋጀት እንዲችሉ የተለያዩ ነፃነቶች ሊጎናፀፍ ይገባል። የፊልም ባለሙያዎች የጋራ ስራ ደግሞ በዘርፉ ለታዩ ችግሮች መላ ለማፈላለግ ዋነኛ መንገድ መሆኑን ባለሙያዎቹ እንደ መፍትሄ ሀሳብ ያቀርባሉ።

የፊልም ባለሙያዎች ስራቸውን በነፃነት እንዲሰሩ የሀሳብና የኢኮኖሚ ነፃነት ሊጎናፀፉ ይገባል የሚሉት የፊልም ባለሙያዎቹ በስራቸው የሚገጥማቸውን የበዛ መሰናክል ለመወጣት ደግሞ እራሳቸውን ዝግጁ ማድረግ ይገባቸዋል። በተጨማሪም አገራዊ ጉዳዮች ለማህበረሰቡ በሚጠቅም መልክ በማንሳት አገራዊ አንድነት ለመፍጠር የሚረዱ የፊልም ስራዎች ማዘጋጀት ላይ ትኩረት እንዲያደርጉም አሳስበዋል።

በፊልም ስራ ባለሙያዎች የተነሱ የሙያተኞች መሰረታዊ ችግር በመቅረፉ በኩል የባለድርሻ አካላት ቅንጅታዊ ስራ አስፈላጊ መሆኑን የጠቆሙት ባለሙያዎቹ፤ለዘርፉ እድገት እና ለውጥ የእነዚህ አካላት ያላሰለሰ ጥረት ወሳኝ መሆኑን ያስረዳሉ። በዚህም የሚገኝ የተሻለ ውጤት አገርና ህዝብ ጠቃሚ እንደሚያደርግ ሙሉ እምነት አላቸው።

አገራዊ ጉዳዮችን በፊልሞቻችን ውስጥ በማካተት ማህበረሰቡ አገሩን እንዲወድና የእርስ በርስ ትብብሩን አጠንክሮ እንዲቀጥል መስራት የፊልም ዋነኛ ስራ ሊሆን ይገባል። በተለይም ማህበረሰቡን አዝናኝ በሆነ መልኩ እያስተማሩ ሁለንተናዊ የሆኑ ማህበረሰባዊ ለውጦች ለማስመዝገብ የሚካሄደውን ጥረት እንዲደግፍና ከኪነ ጥበብ ዘርፎች አንዱ የሆነው ፊልም የሚጠበቅበትን ማበርከት እንዲችል ትኩረት ሊሰጠው ይገባል።

የህይወት ገጽታ

«ኢትዮጵያ ከመቼውም በላይ የተስፋ አየር መተንፈስ የሚያስችላት አሰላሳዮችን ትፈልጋለች»

ኡዝታዝ ያሲን ኑሩ

ጽጌረዳ ጫንያለው

በጎነት እንድሰራ ከፈጣሪ የተቸረኝ ነው ቢሉም በጎነታቸው የአምባሳደርነት ማዕረግን ከጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር አብይ አህመድ አስከመቀበል አድርሷቸዋል፡፡ በአረንጓዴ ልማት ሥራቸውም እንዲሁ አምባሳደር ሆነዋል፡፡ ሃይማኖታቸውን የሚጠብቁና የሌሎችንም ሃይማኖቶች የሚያከብሩ የሃይማኖት መምህር፣ በእያንዳንዱ ንግግራቸው ሰው የሚማርባቸውም ናቸው፡፡ ብዙዎችን አንድ ከማድረግ ጋር ተያይዞ ብዙ የትምህርት ሲዲዎችን ስማስተማሪያነት አበርክተዋል፡፡ በተለይ የሚታወቁት በተለያዩ መድረኮች ላይ በሚያደርጓቸው አአምሮን አነቃቂ በሳል ንግግሮቻቸው ነው፡፡ ይሄ መልካምነታቸው፣ ከራሳቸው አና ዙሪያቸው ውጪ ስሌሎችም አሳቢነታቸው ስብዙዎቻችን ትምህርት ይሆናልና አርአያ ይሆኑን ዘንድ ስዛሬው ፪፪የሕይወት ገጽታ« አምድ አንግዳችን አድርገናቸዋል - የሃይማኖትና የሲደርሽፕ መምህሩን ኡዝታዝ ያሲን ኑሩን፡፡



ፎቶ - ፀሐይ ንጉሤ

አብዮቱ

የተወለዱት አርባራቱ ታቦታት አሉባት ከምትባለው፤ በሃይማኖት ተከባብሮ መኖር ከሚቻልባት ጎንደር ከተማ ጢያሳ ላይ ነው። እናም በዚህች ከተማ የሃይማኖትን የመዋደድ ጥግ አይተው ነው ያደጉት። በ1971 ዓ.ም የተወለዱ ሲሆን፤ ለአብዮቱ በተጠጋጋ ጊዜ ስለነበር በአስገራሚ ሁኔታ ውስጥ አልፈው ነው ይህችን ዓለም የተቀላቀሉት። የአጎቶቻቸው የኢህአፓ አባል መሆንና መፈለግ ከእናታቸው ምጥ ጋር እኩል ገጠመ። ሁሉን ልጅ ሲወለድ ሆኖ የማያውቀው ከስተትም በእንግዳችን መወለድና አለመወለድ ላይ ጥላ አጣላ።

በዚህም የአካባቢው ሰው ተሰብስቦ በምጣቸው ተጨንቆ ግራ ተጋባ፤ ምን ማድረግ እንዳለበትም ግራ ገባው። በሰላም እንዲገላገሉም በየእምነቱ መጸለዩን ተያያዘው። አንዱን ውጥረት ሳይወጡት ግን ሌላ ድንገተኛ ዱብዳ መጣባቸው። ጀኔራሉ ከእነ ወታደሮቹ በቤት ውስጥ ሰተት አለ። «ምንድነው ስብሰባው» ሲልም ጠየቀ። ሁሉም በፍራቻ ውስጥ ሆነው «ምጥ ይዟት ነው» ሲሉ መለሱ። እናቲቱ በምጥ ተይዛ ስትጮህም አያት። ወዲያውም አዘነላት። በጀኔራሎችና በወታደሮች ታጅበውም ሆስፒታል ተወሰዱ። በወቅቱ ዶክተሮቹ ሳይቀር እየተሯሯጡ ነው የተቀበሏቸው። ምክንያቱም የጀኔራሉ ሚስት መስለዋቸዋል።

እንግዳችን እስኪወለዱ ድረስ ከቦታው ሳይርቅ ጠበቀና መወለዱን ሲሰማ ትልቅ እስኪሆኑ ድረስ የሚጠሩበትን ስም አወጣላቸው። ይህም በአብዮቱ ወቅት ስለተወለደ አብዮቱ በሉት ያለው ነው። የጀኔራሉን ትዕዛዝ አለመቀበልና አለማድረግ አደጋው የከፋ ነውና ከዚያች ቀን ጀምሮ የእንግዳችን ስም አብዮቱ ሆኖ ቀጠለ። አሁንም ቢሆን በዚህ ስም የሚጠሯቸው በርካቶች እንደሆኑ አጫውተውናል።

እንግዳችን በባህሪያቸው አትንኩኝ ባይ፤ ረባሽ፤ መታዘዝ ልዩ ባህሪያቸው የሆነ፤ መሮጥና ኳስ መጫወጥ እንዲሁም ዋና መዋኘትን አጥብቀው የሚወዱ ናቸው። ቤተሰብ ነፃ አድርጎ ያሳደጋቸው በመሆናቸው ደግሞ ከጓደኞቻቸው ጋር ሃይማኖታዊ ቦታዎች ላይ ሳይቀር ያሻቸውን የሚያደርጉም ጭምር። በተለይ የማይረሳቸው ፋሲል ግንብ ውስጥ ያለው ገንዳ ውስጥ ሳይቀር ይዋኙ የነበረበት ነው። ግን ተለቅ ሲሉ ጸበል መሆኑን ተረዱና የእምነት ልኬቱን ላለማለፍ ብለው እንዳቆሙት አጫውተውናል።

አብዮቱ በዙሪያቸው በርካታ ቤተክርስቲያናት በመኖራቸው ቅዳሴውንና መዝሙሩን እየሰሙም ነው ያደጉት። ልዩነቱ የሰፋም አልነበረም። አንዱ አንዱ ቤት ሄዶ መብላት፤ ያለውን መጋራት፤ መተዛዘን ብቻ ነው የሚያውቁት። እንዲያውም ሌላው ከልጅነት ትዝታቸው የማይረሱት መደጋገፉን እንደሆነ ነግረውናል። እርሳቸውም በዚህ ተሰርተው ማደጋቸው ያስደስታቸዋል። እንዲያውም ይህ ሁሉ እሴቶቻችን ቢፈተሽ ትውልዱ የሚማርበት ብዙ ነገር ያገኛል ብለው ያምናሉ።

«የተላከ አፉን ለከከ» እንደሚባለው እንግዳችን ጎረቤቱን የሚያግዙት በመላላክ ነው። ይህን የሚያደርጉት ደግሞ ጉርሻ ፍለጋ አልነበረም። መሮጥና መመረቅ ስለሚያስደስታቸው ነው። በዚያ ላይ አባታቸው ነጋዴና ከሰፈሩ የተሻለ የኢኮኖሚ ደረጃ ላይ ስለሚገኙ እርሳቸውን ብቻ ሳይሆኑ የሰፈሩ ሰው ጭምር እንዳይቸገር ያግዛሉ። እንዲያውም ለዕቃ ግዢ ሌላ ቦታ ሄደው ሲመጡ የማያመጡላቸው ነገር የለምና የሚያከብሯቸውና የሚያመሰግኗቸው ብዙ ናቸው። እንግዳችንም ቢሆኑ የመጣውን ሲያከፋፍሉ ብዙ ምርቃት ስለሚያገኙ የሚደሰቱበት ጊዜ ይህ እንደነበር ያስታውሳሉ።

ያሲን የመጽሐፍ (የኪታብ) ስማቸው ሲሆን፤ ይህ እንዲሆን የፈቀዱበት ምክንያት ያሲን ማለት ከነብዩ መሀመድ መጠሪያ ስም አንዱ በመሆኑ፤ የቁርአን አንዱ ክፍል፤ ምዕራፍና የሰው ልጅ ከፈጣሪ ጋር መነጋገርና ከእርሱ እንዲሰጠው የሚፈልገው ነገር ካለ እንዲፈጸምለት የሚቀራው የመጽሐፍ ክፍል በመሆኑ ተወዳጅነቱ ስለላቀባቸው ነው።

ኡዝታዝ በመሆናቸውም ያንን ህልም እውን ለማድረግ ይሻሉና ነው። እንግዳችን «ልጅነቴ በርካታ ነገሮችን ሰጥቶኛል። የመጀመሪያው ደግሞ አለመበለጥን ነው። ታግዬ ብዙ ነገሮችን እንዳሸንፍ፤ ያቀድኩትን እንድፈጽም ብርታት ሆኖልኛል። የይቻላል መንፈስን አላብሶኛል። አብሮ መኖርን ባህሪዬ እንዲሆን አድርጎልኛል» ይላሉ። በዚህም እየኖሩበት እንደሆነ ይገልጻሉ።

ከጎንደር እስከ አዲስ አበባ

ትምህርታቸውን «ሀ» ብለው የጀመሩት በቀዳማዊ አጼ ኃይለሥላሴ ትምህርት ቤት ነው፤ በክፍል ውስጥ ትምህርታቸውን ጉብተው በሚገባ ስለማይከታተሉ ሰነፍ ከሚባሉት ተማሪዎች ተርታ ይመደቡ ነበር። እንዲያውም አንደኛ ክፍል ደግመው እንደነበር ያስታውሳሉ። ጨዋታ ከመውደዳቸው አንጻርም ትምህርታቸውን ትኩረት አይሰጡትም። ጻዲቁ ዮሐንስ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ሲገቡ ግን ትንሽም ቢሆን ለውጥ እያሳዩ መጥተዋል። በዚህም ትምህርት ቤት እስከ ስድስተኛ ክፍል መማር ችለዋል።

ቀጣዩ የትምህርት ጉዟቸው አጼ ፋሲለደስ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ሲሆን፤ ሰባተኛና ስምንተኛ ክፍልን ብቻ ነው የተማሩት። ጎን ለጎን ግን ከትምህርት በኋላ ቁርዓን ቤት በመሄድ ቁራንም ይቀሩ ነበር። ከዚያ ደግሞ አጼ በካፋ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤትን ተቀላቀሉ። ከዘጠኝ እስከ 12ኛ ክፍል መማር ቻሉ። እንዲያውም ይህንን ትምህርት ቤት ጥንካሬያቸው የመጣበትና ማንነታቸው የተስተካከለበት እንደነበር ይናገራሉ። ለዛሬ ማንነታቸው መሠረት መያዝ የጀመሩበት ስለሆነም በጣም እንደሚወዱት አጫውተውናል።

በሁሉም የትምህርት ደረጃዎች አንድ ነገር ባህሪያቸው እንዳልነበር የሚያነሱት ባለታሪኩ፤ ያነበቡትን ብዙ ጊዜ እያስታወሱ መቆየት አይችሉም። ግን ወዲያው ለመመለስ ከሆነ ማንም አያክላቸውም። እናም እስከ 12ኛ ክፍል ሲዘልቁ በዚህ ሁኔታ እንደተጓዙ ያወሳሉ። ከ12ኛ ክፍል ማጠቃለያ ፈተና በኋላ ደግሞ ከአካባቢያቸው ሳይርቁ ጎንደር ዩኒቨርሲቲ በመግባታቸው ብዙ የተሻሉ ነገሮች እንደገጠሟቸውም ይናገራሉ። በዚህም በዩኒቨርሲቲው በቢዝነስ ማኔጅመንት የትምህርት መስክ ዲፕሎማቸውንም ሆነ ዲግሪያቸውን ይዘው መመረቅ ችለዋል።

ሌላኛው የትምህርት ምዕራፋቸው የሚወስደን ሸገር ላይ ሲሆን፤ ቀን እየሰሩ ማታ ለመማር አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲን ነበር የተቀላቀሉት። በዚህም ኢኮኖሚክ ለመማር ሞከሩ። ሆኖም ከዓመት በላይ ትምህርቱን መከታተል አልቻሉም። ምክንያቱም ከቁጥር ቅመራው ጋር አልተመቻቹም። የትምህርት ፍቅሩም በዚህ ዘርፍ ላይ ብዙም አልጣማቸውም። ስለዚህም ትምህርቱን አቋረጡት። ግን መማር ብቻ እንደሚያሻግራቸው ያምናሉና በተለያዩ ሥልጠናዎች አቅማቸውን ካጎለበቱ በኋላ ዳግም ለመማር «በአይ ኤል አይ ኢንተርናሽናል ሊደርሽፕ ኢንስቲትዩት» ተመዘገቡ። በኦርጋናይዜሽናል ማኔጅመንትም ሌላ ዲግሪያቸውን ሰሩ።

ቀጥለው ደግሞ በእንግሊዙ «ግሪኒዊች ዩኒቨርሲቲ» ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በትራንስፎርሜሽናል ሊደር ሽፕ መማር ጀምረው መመረቂያ ጽሑፍ እያዘጋጁ ሳለ ለእስር በመዳረጋቸው ምክንያት ሳይጠናቀቅ ቀረ። እናም ዳግም ከትምህርት ጋር የተገናኙት ከአራት ዓመት የማረሚያ ቤት ቆይታ በኋላ ሆነ። በፕሮጀክት ማኔጅመንት መመረቂያ ጽሑፋቸውን እያዘጋጁ ሲሆን፤ ጎን ለጎን ሦስተኛ ዲግሪያቸውን በኦርጋናይዜሽናል ማኔጅመንት «በ ኢንተርናሽናል ኢስላሚክ ዩኒቨርሲቲ አፍ ማሊሲያ» እየተማሩ ይገኛሉ። ኢንተርናሽናል አሜሪካን ፕሮጀክት ማኔጅመንት ዩኒቨርሲቲ ኢንተርናሽናል ፕሮጀክት ማኔጅመንት ሰርቲፋይድም ሆነዋል። ከዚህ ተሻግረውም በተለያዩ ሥልጠናዎች እውቀታቸውን እያዳበሩ ናቸው።

ՀԱՅԿԱԿԱՆ ՀԱՄԱՅՆՔ



ԳԵՂԱՐՎԵՍՏԻ ՀԱՅԿԱԿԱՆ ՀԱՄԱՅՆՔԻ ՄԱՆԿԱՊԱՐՏԵԶԸ ՀՅՈՒՐԱՍՊԵՍ ԱՐԱՄ ՄԱՐՏԻՐՈՍՅԱՆԻ ՀԱՆԴԵՊ ՀԱՅԿԱԿԱՆ ՀԱՄԱՅՆՔԻ ՆԱԽԱԳԱՀ ՊԱՐՈՆ ՎԱՀԱՆ ՍԱՐԳՍՅԱՆԻՆ ԵՎ ՀԱՅԿԱԿԱՆ ՀԱՄԱՅՆՔԻ ՄԻՋՈՑԱՌՈՒՄՆԵՐԻ ՆԱԽԱՐԱՐ ՀՐԱՆՏ ՎԱՐԴԱՆՅԱՆԻՆ ՀԱՆԴԻՊԵԼ ՀԵՏՈ։

ՀՀ ՄԵՋ ԿՅԱՆՔ

ՄԵՐ ՀԱՅՐԵՆԻՔԸ ՄԵՐ ՄԱՅՐԱՔԱՂԱՔՆ Է

ՀՀ ՄԵՋ ԿՅԱՆՔ



ባህልና ቱሪዝም

ወመዘክር የእኛነታችን መገለጫ ጓዳ

አስመረት ብስራት

በኢትዮጵያውያን ባህላዊ ቁሳቁሶች አሸብርቋል። መቀመጫዎቹ በእንጨት የተሰሩ ባህላዊ ሶፋዎች ናቸው።በእንጨት ተሰርቶ በተቀመጠው ሶፋ ላይ የሚታዩት ዲዛይኖች ቀልብ ይስባሉ። ቁጭ ብዬ ዙሪያ ገባዬን ተመለከትኩ ትንሽ ዘመናዊ እቃዎች የተቀላቀሉበትም ቢሆን የእኛነታችን መግለጫ የሆኑት ቁሳቁሶች ጎልተው አይንን ይይዛሉ።በግድግዳው ላይ የአክሱም፣ ላልይበላና የፋሲል ግንብ ስእል ልዩ ውበት አላቸው። ይሄንን የተመለከትኩት በኢትዮጵያ ብሄራዊ ቤተመዘግበትና ቤተመፃህፍት ኤጀንሲ ዋና ዳይሬክተሩ ቢሮ ብቅ ባልኩበት ወቅት ነው።

ባህላዊ ታሪካዊ ቁሶችና ስዕሎች በቅጽበት ሀገሬን እንድጎበኛት ፈቅዷል። በቤት ውስጥ ስራ የሚታወቁት ሴቶች ባለሙያነታቸውን ሰዓሊያን በብሩሻቸው አስቀርተዋል። ጥንታዊ ሃይማኖታዊ ትምህርት ከአባት ወደ ልጅ እንዴት ይንቀረቀራል ቢሉ ግድግዳው ላይ የተሰቀለውን ስዕል በማየት ብቻ መልስ ማግኘት ይቻላል። ከእግር ስር ተቀምጦ የሚነበብለትን የሚያዳምጠው ልጅ ባህላዊ የትምህርት ቅብብሎሹን ለማስታወስ ያግዝ ይመስለኛል። በስርአት የመዝገብ አቃፊ ውስጥ የተደረደሩት ሰነዶች ላይ አረንጓዴ ቢጫ ቀይ ቀለማት የሀገራችን ቁጥሮች ተፅፈው ይነበባሉ። የኢትዮጵያን ተዝቆ የማያልቅ ባህልና ታሪክ ተሸክሞ ማንነታችንን በማይገልጹ ቁሳቁሶች የተዋቡ የመንግስትና የግል ቢሮዎችን በአይነ ህሊናዬ አስታውሼ በቁጭት ተንገበገብኩ ያለንን ለሌላ የሚተርፍን ሀብት የማንጠቀም ንፉጎች ነን እያልኩ ራሴንም ከመውቀስ አልዳንኩም። ምክንያቱም ቤት ማስዋቢያ ታሪክ፣ ባህልና ሃይማኖትን መዘከሪያው አንዱ መንገድ ቢሆንም ዋጋ አለመስጠታችን አሁንም ያንገበግባል።

ያሉንን ቅርስ አቧራ አራግፈን ሀብት ማድረግ፣ ታሪካችንን ባህላችንን በየኢጋጣሚው ማስተዋወቅ ትንሽ ሰርተን ብዙ የምናተርፍበት ነው። አሁን አሁን የምናያቸው የራሳችን መታወቂያዎች ዋጋ እንዳሳጣናቸው ይሰማኛል። ቀሲቃሽ ፣አነሳሽና ተነሳሽ ካለ ሀብቱ በየቢሮአችን አለ። አምረንበት ተውበንበት ሌላውንም እናስደስታለን።

የኢትዮጵያ ብሄራዊ ቤተመዛግበትና ቤተመፃህፍት ኤጀንሲ ዋና ዳይሬክተር የአቶ ይኩኖአምላክ መዝገቡ ቢሮ ታዲያ ለሌሎች አርአያ በሚሆን መልኩ በተለፋ ቆዳና በእጅ በተፈለፈለ እንጨት ድብልቅ ያጌጠ የእንጨት ወንበሮች ፣ጠረጴዛ ሌሎች በጣም ውብ ቁሳቁሶች እውነትም የሰነድ ማከማቻ፣ የታሪክ መገለጫ የባህል ማስታወቂያ እያልኩ ለራሴ በራሴው ነገረኩት። ይህን እያወጣሁና እያወረድኩ ተጨማሪ መረጃዎችን አገኝ ዘንድ ከአቶ ይኩኖአምላክ ጋር ወመዘክር ስራውን የጀመረው መቼና እንዴት ባለ ሁኔታ ነው በማለት የቃለመጠይቅ መነሻ ጥያቄዬን አቅርቢ ወደ ዋናው ጉዳይ ገባሁ።

አቶ ይኩኖአምላክ እንደነገሩኝ የህዝብ ቤተመፃህፍት (ወመዘክር) በሚል ስም የተቋቋመው በንጉሰ ነገስቱ ዘመን ነው።በአፄ ሀይለስላሴ የግል መፃህፍት ስጦታ አገልግሎት መስጠት ጀመረ። ከዛ በኋላ አገልግሎትን እያስፋፋ አሁን እስካለው ድረስ ተጉዟል። አሁን የሰባ ስድስት አመት እድሜ ባለፀጋ የሆነው ወመዘክር በርካታ መፅሃፍትን በጉያው ይዞ ለትውልድ ባህልንና ታሪክን ሰንዶ እውቀት የመመገብ ስራውን እያከናወነ ይገኛል።

በአሁኑ ሰአት በግቢ ውስጥ ስምንት ቤተመፃህፍት አሉ። አንደኛው ሰፋ ያለና ትልቅ የህግ ክምችት ቤተ መፅሀፍ ነው።ይህ ቤተ መፅሀፍት በኢትዮጵያ ላይ የተፃፉ ማንኛውንም ፅሁፎች ከሀገር ውስጥም ሆነ ከውጭ ስለ ሀገራችን የተፃፉ ፅሁፎች የሚሰበስብ ነው። ይህ ማለት ጋዜጦች፣ መፅሄቶች፣ የጥሪ ካርዶች፣ በራሪ ወረቀቶች... በሙሉ በመሰብሰብና ለጥናትና ምርምር ለሚፈልጉት ሰዎች ለማቅረብ የተደራጀ ክፍል ነው። ይሄ ክፍል በአብዛኛው ለማቆያነትና ለትውልድ ለማስተላለፍ የተደራጀ ነው።



በኤጀንሲው ከሚገኙ ታሪካዊና ሃይማኖታዊ ቅርሶች አንዱ



ሁለተኛው ዋና ክፍል የህዝብ ቤተ መፃህፍት ይባላል። የህዝብ ቤተ መፃህፍት ደግሞ አጠቃላይ ለማጣቀሻ የሚሆኑ መፃህፍት የሚገኝበት ነው። በዚህ ቤተ መጽህፍት ውስጥ የተለያዩ አጋዥ ትምህርት ነክ መፅህፍቶች ይገኛሉ። በብዛት የሚገለገሉበት የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች በመሆናቸው መፅህፍት ሲገዛ በአንባቢያን ፍላጎት ያገናዘበ ስለሚሆን በአብዛኛው ትምህርትና ትምህርት ነክ መፅህፍቶችን የያዘ ቤተ መፃህፍት ነው።

ሶስተኛው የኢትዮጵያ ጥናት ቤተ መፃህፍት የሚባል ክፍል ነው።ይህ ክፍል ከህግ ክምችቱ በተለየ ሁኔታ በውጭ ሰዎችም ሆነ በሀገራችን ፀሃፍት ኢትዮጵያን አስመልክቶ የተፃፉ ፅሁፎች የሚነበቡበት የኢትዮጵያ ፅሁፎች ለአገልግሎት የሚቀርብበት ክፍል ነው።

አራተኛው ጥንታዊ የብራና መፅህፍት ያሉበት ቤተ መፃህፍት ነው። በዚህ ጥንታዊያን የብራና መፃህፍት በአካል የሚነበብበት ቦታ ነው። በብዛትም ሆነ በጥራት ከአህጉራችን አፍሪካ ቀዳሚ ሊያደርጉ የሚያስችሉ መፅሃፍት ስብስብ ያለበት ክፍል ነው። ከፍሉ በመጠኑ አነስ ያለ ቢሆንም እዛ ውስጥ"እሳተከላ" በሚባል እሳት የማያቃጥለው ካዝና ውስጥ ነው የሚቀመጡት። በእዚህ ክፍል በስጦታ የመጡ አሉ፤ በዩኔስኮ የተመዘገቡ የፅሁፍ ቅርሶችም ይገኙበታል። እነዚህ ቅርሶችም ተጠብቀው እንዲቆዩና ታሪካዊ ዳራ እንዲኖራቸው ተደርጓል።

አምስተኛው ጥንታዊ የብራና ፅሁፎች ከኢትዮጵያ ከሚገኙ ገዳማትና ከየመስኪዶቹ የተሰባሰቡ መፃህፍቶች በማይክሮ ፊልም ቴክኖሎጂ የሚነበበበት ክፍል ነው።በእርግጥ የማይክሮ ፊልም ቴክኖሎጂ በአለም ላይ እየቀረ የመጣ ቴክኖሎጂ ቢሆንም በእኛ ሀገር በተወሰነ ደረጃ ፅሁፎችን በድጂታል ተቀይሮ የቀረው በማይክሮ ፊልም እየተነበበ ነው።በዚህ ክፍል ብዙ ሺ ኮፒዎች ይገኛሉ።

ሌላው የህፃናት ቤተ መፃህፍት ነው። የህፃናት ቤተ መፃህፍት ውስጥ ከሁለተኛ ደረጃ በታች ያሉ ህፃናት፤ ወላጆቻቸው አብረዋቸው እስካሉ ድረስ የእድሜ ገደብ በማይኖረው ሁኔታ ህፃናት የሚገለገሉበት ቤተ መፃህፍት ነው። ይህ ክፍል አንባቢ ትውልድን ለማፍራት ታስቦ የተዘጋጀ ሲሆን ማንኛውም ልጅ በክፍል ደረጃው የተዘጋጀውን መፅሃፍ ወስዶ መገልገል ይችላል።

ሰባተኛው ክፍል ለአይነ ስውራን አገልግሎት የሚሰጠው ቤተ መፃህፍት ነው። ይህ ክፍል ለየት ያለ ሲሆን በተለያዩ ቴክኖሎጂ የተሟላና በብሬል የሚያነቡበት ክፍል ነው። በተጨማሪም የተሻለ አገልግሎት ለመስጠት መፅሀፍትን በድምፅ አስቀርፆ ለማስቀመጥ ከኢትዮጵያ አይነስውራን ብሄራዊ ማህበር ጋር በመተባበር እንቅስቃሴ ተጀምሯል። ኤጀንሲው በራሱ አስቀርፆ ከሚያስቀምጣቸው መፅሀፍት በተጨማሪ የተቀረፁና በሬዲዮ ሲተላለፉ የነበሩ መፅሃፍትን ከሸገር ኤፍኤም ለመቀበልና ለእነዚህ የህብረተሰብ ክፍሎች ለማቅረብ መስማማታቸውን ይናገራሉ ።

ስምንተኛው የድምፅና የምስል ቤተ መጽሀፍ በመባል ይታወቃል። ክፍሉ በድምፅና በምስል ያሉ ነገሮችን የሚያቀርብ ቢሆንም በጣም የሚያኮራ በሚያስብል መልኩ ስብስብ የለውም። ይህን ክፍል ሙሉ ለማድረግ ከመገናኛ ብዙሃን ጋር የመስራት ሙከራ አለ።ይህ ሲደረግ የመገናኛ ብዙሃንን መብት የሚጣረስ ተግባር ሊሆን ስለሚችል የነሱን መብት በማይነካና ኤጀንሲው «ማንኛውም በምስል፣ በድምፅ፣ በድምፅና ምስል የተቀረፀ ነገር ሁሉ የመያዝ መብት አለው» የሚለውን መብቱን በመጠቀም ለጥናትና ምርምር አገልግሎት ብቻ እንዲውሉ የማድረግ ስራውን ለማጠናከር ታቅዷል።

ከስምንቱ ቤተመፃህፍት በተጨማሪ ቤተመዛግብት በኤጀንሲው ውስጥ ይገኛል። ይህ በጣም ትልቅ የሚባል ሲሆን እዚህ ክፍል ውስጥ ያሉት የፅሁፍ ቅርሶች የመንግስትን ውሎዎች የሚዘግቡ፤ የመንግስት ስራዎች ከ130 አመት በፊት የነበሩ መዛግብትን የያዙ ናቸው። ሌላው የግለሰብ ደብዳቤዎች ማለትም በመንግስት ከፍተኛ ቦታ የነበራቸው በየስማቸውና በየሚኒስቴር መስሪያ ቤታቸው ስም የተፃፉ ደብዳቤዎች በዝርዝር ተቀምጠዋል። ይህ ደግሞ ሀገራችንን ከአፍሪካ በቀዳሚ ተርታ ማሰለፍ የሚችል የፅሁፍ ሀብት ያላት ሀገር ለመሆን እንድትችል አድርጓታል። ይህን ስራ በስፋት ለማከናወን እንዲቻል በአሁኑ ወቅት 13 ፎቅ ያለው ህንፃ እየተሰራ መሆኑን ዋና ዳይሬክተሩ ይናገራሉ። ህንፃው እስከሚጠናቀቅ በግምት ግማሽ ቢሊየን ብር እንደሚያወጣ ይገመታል። ግንባታው ተጠናቆ ስራ ሲጀመር በአፍሪካ ካሉት አቢያተ መፃህፍት ትልቁ ሊያደርገው የሚችል ነው። ህንፃው ብቻ ሳይሆን ህንፃው ውስጥ የገቡ ጥንታዊ ሰነዶች ጭምር ናቸው አንድ ላይ በመሆን ታላቅነቱን የሚያሳዩት ።

ጥንታዊ ፅሁፎቹ ያሉበት ክፍል በጣም ትንሽ ቢሆንም ከአደጋ ለመጠበቅ እዛ እንዲቆዩ የተደረገ መሆኑን ጠቅሰው፤ ለወደፊት በአዲሱ ህንፃ ላይ ሰፊ ቦታ ይኖረዋል። መንግስትም ለዚህ ጉዳይ ትኩረት መስጠቱ ያስመሰግነዋል ሲሉ ይናገራሉ።

ኤጀንሲው የአገልግሎት አሰጣጡን ቀልጣፋ ለማድረግ ከኮቪድ 19 መከሰቱ በፊት የ24 ሰአት አገልግሎት መስጠት ጀምሮ እንደነበር የሚያስታውሱት አቶ ይኩኖአምላክ ይህ አገልግሎት ከጠዋቱ ሶስት ሰአት እስከ ንጋቱ አንድ ሰአት ከፍት ሆኖ በቀረው ሁለት ሰዓት ውስጥ የፅዳትና የሽልፍ ስራ ይሰራል። ይሄን ስራ የተሳካ ለማድረግ ከቡና ጠቅላይ ሚኒስትሩ ጋር በፃፍነው ደብዳቤ በአንድ ሳምንት መልስ ተሰጥቶት እየተሰራ ቆይቷል። ለዚህም ቤተ መፅሀፍቱ ባለውለታነታቸውን አይዘነጋም ብለዋል ። ምንም እንኳን የ24 ሰዓቱ አገልግሎት እንደተጀመረ ብዙ ሳይቆይ በሽታው ቢከሰትም የተሞከሩ ነገሮች ግን ውጤታማ እንደነበሩ ያስታውሳሉ።

የንባብ ባህልን ከማበረታታት አንፃር በርካታ ስራዎች እየተሰሩ መሆኑን ዋና ዳይሬክተሩ ይናገራሉ። ከተሰሩት ስራዎች መካከል ለዋና ዋና ኮቪድ ማእከላት ማለትም ለአዲስ አበባ፣ለአማራ፣ ለትግራይ፣ ለኦሮሚያ ክልል እና ድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር በርካታ መጽሀፍት መውሰዳቸውን ገልጸዋል። ሌላ ዋናው ስራ በአዲስ አበባ በተለይ የኮንዶሚኒየም ቤቶች በሚገኙበት ቦታ አቢያተ መፃህፍት አሉ።እነዚህ በኤጀንሲው እገዛና የኮንዶሚኒየም ነዋሪዎች የጋራ መገልገያቸውን ለቤተ መፃህፍት አገልግሎት በመስጠታቸው የተሳካ መሆኑን ጠቅሰዋል። አምስቱ በጎተራ፣ጆሞ አንድ፣ ጎፋ፣ ባልደራስ እና ቀራኒዮ በተጨማሪ በቅርቡ ደግሞ ልደታ ኮንዶሚኒየም ስራ ለመጀመር ተስማምተው እየተንቀሳቀሱ መሆናቸውን ያስረዳሉ።

መፅሀፍቱን ከማቅረብ በሻገር በኮቪድ ምክንያት ቤተ መፅሀፍቱ በመዘጋቱ የተነሳ ቤታቸው ያሉ የኤጀንሲው ሰራተኞች በአቅራቢያቸው በሚገኙ ቤተ መፃህፍት እንዲያገለግሉ ተደርጓል። በመፃህፍት ውሰት ምክንያት በሽታው እንዳይተላለፍም መጽሀፍቱ ከተመለሱ በኋላ በካራንታይን ሽልፍ ላይ በመደርደር አቆይቶ በድጋሚ የማዋስ ስራ ይሰራል። በየቤተ መፃህፍቱ ጋዜጦች ፣የልጆች መፃህፍት፣አጋዥ መፃህፍትም ይቀርባሉ። ከዚህም ባሻገር በመገናኛ ብዙሃን የንባበ ንቅናቄዎችን የመፍጠር ስራዎች እየተሰሩ ሲሆን በየፕሮግራሞቹ ላይ ታላላቅ ፀሃፍት በመገኘት የንባብ ንቅናቄ ይፈጥራሉ።

ሌላው ዋና ዳይሬክተሩ የተናገሩት በዩኒቨርሲቲዎች ያሉ የንባብ ክበብ አባላት ከዩኒቨርሲቲ ወደ አዲስ አበባ የመጡት ክበባትን የንባብ ቦታና መፅሃፍትን በማቅረብ የንባብ ባህል እንዳይጠፋ ተደርጓል። በአን ላይን ንባብ ለማድረግ ታቅዶ የቆየ ቢሆን በሀገሪቱ የህትመት ኢንዱስትሪ በስፋት እየታተመ ስለጥራት ትኩረት እየተሰጠ ባለመሆኑ የተነሳ ይህን ለመቆጣጠር ለጊዜው የዘገየበት ሁኔታ አለ።

ኤጀንሲው በቴክኖሎጂ የታገዘ የንባብ ባህል እንዲኖር ኤል ኣርምስ የተባለ ፕሮጀክት በመስራት ላይ ነው። ኢንተግሬትድ ላይብረሪ ኤንድ አርካይቭ ማኔጅመንት ሲስተም በስድስት ወራት ውስጥ ተጠናቆ የሚመረቅ ይሆናል ። ይህ ማለት በቤተ መፃህፍቱ ቅጥር ግቢ ብቻ መፃህፍትን ዳውን ሎድ ሳያደርጉ ለማንበብ የሚያስችል ነው።

የኮሮና መከሰት የፈጠረውን ምቹ አጋጣሚ በመጠቀም አገልግሎቱን በቀጣይ ለማሻሻል ግንባታ እየተከናወነ ነው። ቀደም ሲል ምግብ ቤቱ ከቤተ መፃህፍቱ ጋር የተቀራረበ በመሆኑ ሊፈጠር ከሚችል አደጋ ለመከላከል በሚል የምግብና የመፅዳጃ ቤት ለብቻው የህንፃ ግንባታ እየተደረገ ነው። እንዲሁም ቤተ መፃህፍቱ ውስጥ የተለያዩ እድሳት እየተደረገ ነው። ከእነዚህ መካከል ጠረጴዛ ላይ የመብራት ሶኬት መስራትና ሌሎች ጉድለቶችን በማስተካከል ደረጃውን የጠበቀ እድሳት እየተደረገ ነው። ይህም የላቀ አገልግሎት ለመስጠት የሚያግዝ መሆኑን አቶ ይኩኖአምላክ ይናገራሉ።

ኤጀንሲው በቀጣይም የስእል ሀብቶችን ለማሰባሰብ ዕቅድ አለው። ቀደም ሲል የአለም ሎሬት አፈወርቅ ተክሌ ይገለገሉበት የነበረውን ክፍል ስእሎቹን በማሰባሰብ አውደ ርእይ ለመሳየትና ሀብቶችን ለማቆየት የሚያስችል ቦታ ለመፍጠር መታሰቡን አስረድተዋል። ግቢው ውስጥም ማንበቢያ ቦታዎችን በማዘጋጀት ስለንባብ ለመወያየት የሚያስችል ሰፊ ቦታ በመስራት የሀገርን ቤተ መዛግብትና ቤተ መፃህፍት በሚመጥን ማእከል እየተቋቋመ ሲሆን፤ ይህ ደግሞ የፅሁፍ ሀብቶቻችንን ለማቆየት አቻ የማይገኝለት ስፍራ ያደርገዋል።

ՎՇՈՒ ԱՍԿՎԱԾԱՅԻ ՀՂԻՖԱՅԱՆՑ -ՀԱՄԱՏԱ

ՀԱՄԱՏԱ

ՀՁԻ ՀԱՄԱՏԱՑ

ՀԱՅԻ ԺԱՄԸ՝ Ինչպե՞ս եք ընդունում ձեր նկատմամբ հնչող մեղադրանքները, թե դուք ձեր ստեղծագործություններում ամեն ինչ չափազանց սև գույներով եք ներկայացնում, ինչպես նաև ձեր հերոսներին ստիպում եք ապրել ծանր պայմաններում:

ՎԱՀԱՆ ՀԱՐՈՒԹՅՈՒՆՅԱՆ՝ Ես ինքս ինձ չեմ համարում ոչ սև, ոչ էլ սպիտակ գրող: Ես ինքս ինձ համարում եմ ոչ ավել, ոչ պակաս, ինչպես որ կյանքն է

ጋመቻመ

ሁኑተኣህ ለወጀህያችመዕ ሩጠኔሂኒ ፈውሯመ ወቻቻሪ ዘጠመ ሂኒ ፈውሯመ ሁኑተኣህ። ሂኒ ሂኒ ሂኒ



ՀԱՐՑԱԽՈՍ

ՀԱՅԱՍՏԱՆԻ ԱԶԳԱՅԻՆ ԹԻՄԸ ՀԱՂԹԱՀԱՐԵՑ ՄԱԼԱՅԶԻԱՅԻ ՀԱՎԱՔԱԶԳԻ ՄՐՑՈՒՅԹԻՆ

ՀՀ ֆուտբոլի ազգային հավաքականի գլխավոր մարզիչ Վարդան Մինասյանը մամուլի ասուլիսում անդրադարձել է Մալայզիայի հավաքականի հետ հանդիպմանը, որը տեղի կունենա հունիսի 7-ին Կուալա Լումպուրում։

«Մենք ամեն ինչ անելու ենք հաղթելու համար, սակայն մեր հակառակորդը ևս ուժեղ է, ինչը ապացուցել է նրանց հաղթանակը Ավստրալիայի հավաքականի նկատմամբ։ Մենք պետք է ամեն ինչ անենք, որպեսզի հաղթենք, քանի որ մեր խնդիրն է հաղթել, ոչ թե հավասարության հասնել»,- ասել է Մինասյանը։

Հիշեցնենք, որ Հայաստանի ազգային հավաքականը հունիսի 7-ին Կուալա Լումպուրում կմրցի Մալայզիայի հավաքականի հետ, իսկ հունիսի 12-ին Երևանում կհանդիպի Ավստրալիայի հավաքականին։

ՀՀ ՖՈՒՏԲՈԼԻ ԱԶԳԱՅԻՆ ՀԱՎԱՔԱԿԱՆԻ ԽԱՂԱՑՈՂՆԵՐԸ

ՀՀ ֆուտբոլի ազգային հավաքականի խաղացողները

ՀՀ ֆուտբոլի ազգային հավաքականի խաղացողները

The Ethiopian Herald
አዲስ ዘመን
Bariisaa SANBATAA
العلم አል-ዓለም
ዘመን
የህትመት ውጤቶቻችንን ለማንበብ
ድረገጻችንንና ፌስቡክ ገጻችንን ይጎብኙ!
የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት
ዌብሳይት፡- www.press.et
ፌስቡክ፡- Ehiopian Press Agency



NG ጋዜጦችና መጽሔቶች ሽያጭና አከፋፋይ
በተጨማሪም ያገለግሉ፡-
- ጋዜጦችን
- ወረቀቶችን
- ቦክስ ፋይል
- ካርትሬጅ
- ብረታ ብረቶችን እንገዛለን።
0933 91 76 91/0913 44 89 00
0922 87 18 52
አድራሻ
ቁ.1 አራት ኪሎ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት ፊት ለፊት

የአዲስ አመት ምኞት

አስመረት ብስራት

ልጆች ! እንኳን ለአዲሱ ዓመት በሰላም አደረሳችሁ ! በአዲሱ ዓመት ምን ምን ተግባራትን ለማከናወን አቀዳችሁ? የ2013 ዓ.ም ምኞታችሁ ምንድነው ያልኳቸው ልጆች «ኮሮና ከሀገራችን ጠፍቶ ትምህርት ቤት ተከፍቶ መማር ነው ምኞታችን » ብለውኛል። እናንተስ?

ካነጋገርኳቸው ልጆች መካከል ተማሪ ናሆም አሰፋ አንዱ ነው። ናሆም የስምንት አመት ልጅ ሲሆን በአዲሱ አመት የሶስተኛ ክፍል ተማሪ ይሆናል። ቅዱስ ሚካኤል ካቴድራል የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚማረው ናሆም ጎበዝ ተማሪ ነው። ናሆም ምኞቱን እንዲህ ሲል ገልፆልኛል“ ለሚቀጥለው አመት ኮሮና ጠፍቶ ትምህርት ቤት መሄድ እመኛለሁ። ሌላው ምኞቴ አጎቴ ለአዲስ አመት ስጦታ ብሎ የገዛልኝን እንቁጣጣሽ ሎተሪ እንዲደርሰኝ ነው ” ብሏል። “ልጆች በአዲሱ ዓመት ትምህርት እንድንጀምር ጤናችሁን ጠብቁ፣ በትምህርታችሁ ጎበዝ እንድትሆኑ መጽሀፍ አንብቡ ” ብሏቸዋል።


ሌላዋ የአዲስ አመት ምኞቷን የገለፀችልኝ ተማሪ በእምነት አሰፋ ትባላለች። በእምነት ሰባት አመቷ ነው። የዩኒቲ አካዳሚ ተማሪ ስትሆን፤ በአዲሱ ዓመት ሁለተኛ ክፍል ትገባለች። ልጆች ! በእምነት በጣም ጎበዝ ተማሪ ናት። ከታናሽ ወንድሟ ከክርስቲያን አሰፋ ጋር ትጫወታለች ፤ የተረት መጽሀፍ ታነባለች። በፊጠራ ስራ ደግሞ የፕላስቲክ ኩባያ መስራቷን ነግራኛለች።

ተማሪ በእምነት ለአዲስ አመት የምትመኘው “ትምህርት ቤት መሄድ ነው። ጓደኞቼን ማግኘትና ኮሮና እንዲጠፋ እፈልጋለሁ “ ብላለች። ልጆች የአፍ መሸፈኛ ማክስ እንዲያደርጉ፣ እጃቸውን በሳሙናና በውሃ ደጋግመው እንዲታጠቡ ትመክራለች። እሷ በእረፍት ጊዜዋ ብዙ የተረት መፅሀፎችን ያነበበች ሲሆን እናንተም እንደሷ ጎበዝ አንባቢ እንድትሆኑ ትመክራችኋለች።

ሌላው ጎበዝ ተማሪ ናታን ኤልያስ ይባላል። ጨዋ ልጅ ነው። ታናሽ እህቱን ፌኔት ኤልያስን በጣም ነው የሚወዳት። ይንከባከባታል፤ ምግብ ያበላታል፤ አብረው ይጫወታሉ።በአርዲ አካዳሚ ትምህርት ቤት የሚማረው ናታን የአንደኛ ክፍል ተማሪ ነው። ናቲ በአዲሱ አመት እናቱ ቃል የገባችለትን ሳይከል እንድትገዛለት ይፈልጋል፤ ኮሮና ጠፍቶ ትምህርት ቤት መሄድ ምኞቱ ነው። “ ሀገራችን ሰላም እንድትሆን እመኛለሁ” ብሏል። ልጆች ሲያድጉ ሀገራቸውን ጥሩ አድርገው መምራት እንዲችሉ ጎበዝ ተማሪ መሆን አለባቸው ሲል መክሯል። እሱም በእረፍት ጊዜው «ኩኩሉ» የምትል የተረት መጽሃፍ ማንበቡን ተናግሯል።

ልጆች ! እናንተም እንደነበእምነት፣ ናሆምና ናታን ለቀጣዩ የትምህርት ዘመን ጎበዝ ተማሪዎች ለመሆን መዘጋጀት አለባችሁ። ረጅም የእረፍት ጊዜ ስላሳለፋችሁ ትምህርቱን እንዳትዘነጉ ማንበብና መፃፍ ተለማመዱ። እሺ !።

አዲሱ አመት የሰላም፣ የጤናና የብልጽግና እንዲሆንላችሁ እንመኛለን።


ተማሪ በእምነት አሰፋ



ለልጆቻችን የምናወርሳቸው ሀብት - ደቅርታ

በጋዜጣው ሪፖርተር

የልጆች ጭንቅላት ነጭ ወረቀት ነው ። የሰጡትን ይቀበላል። የተቀበለውን ይተገብራል። ልጆች ያዩትንና ያደመጡትን በተግባር ለማየትና ለማሳየት ይሞክራሉ። ልማቱንም ሆነ ጥፋቱን በልጅነታቸው የሚወርሱት ከቤተሰባቸው ነው። ልጆች ፊት የሚደረጉና የማይደረጉ ፣ የሚነገሩና የማይነገሩ ነገሮች መኖራቸውን ወላጆችና አሳዳጊዎች ጠንቅቀው ማወቅ እንዳለባቸው የስነልቡና ባለሙያዎች ይመክራሉ። የዚህ ዋናው ዓላማ ልጆች ሁሉንም የተመለከቱትን ነገር ስለሚሆኑ ነው። እናም ለልጆቻችን ጥሩ ጥሩውን ፤ ሊጠቅማቸውና ሊያስተምራቸው እንዲሁም ለሌሎች ሊያስተምሩ የሚያስችላቸውን እውቀት መግበን ማሳደግ ከወላጆች ይጠበቃል። ልጆች በአብዛኛው የቤተሰባቸውና የአሳዳጊያቸው ብሎም የአካባቢያቸው ስራ ውጤቶች መሆናቸው ሊዘነጋ አይገባም።

ሰዎች አንድ ላይ በሚያሳልፉበት በቤተሰብ፣ በትምህርት ቤት፣ በስራ ቦታ ፣ በእምነት ተቋማትና በሌላ በሌላም ቦታ ግጭቶች ሊፈጠሩ ይችላሉ። አዋቂ የምንላቸው ሰዎች በተለያየ ምክንያት ይጣላሉ። ልጆች እርስ በራሳቸው ይጋጫሉ። ይሄ የነበረ፣ አሁንም ያለ፣ ወደፊትም የሚኖር የሰዎች ባህሪ ነው። ታዲያ እንዲህ አብሮን የሚኖርን የሰው ልጅ ባህሪ እንዴት አድርገን ነው ወደ ሰላማዊ መስመር ወደ ፍቅር የምንቀይረው የሚለውን መመልከት ላይ ነው ቅድሚያ ሰጥተን መስራት የሚጠበቅብን።

ልጆች በቤት ውስጥ እርስ በራሳቸው ሲጫወቱ እንኳን በሚከሰት ጸብ መሀል የወላጆች ሚና መሆን ያለበት የጸቡን ምክንያት ምን እንደሆነ ልጆቹን ተራ በተራ እያነጋገሩ ማወቅ፣ ጉዳዩ ቀላል መሆኑን ጸብ ደረጃ ሳይደረስ በመንገርና በመደማመጥ ብቻ መፍታት የሚችሉት እንደነበር ማስረዳት ፤ ከዛም አጥፊው ልጅ የተጣላውን ልጅ ታላቁም ይሁን ታናሹ ብቻ ይቅርታ እንዲጠይቀው ማድረግና ወደ ሰላማዊ ፍቅራቸው መመለስ ነው።

አንዳንድ ቤተሰቦች ወይም ወላጆች ግን በልጆች መካከል ጥል ሲፈጠር የሚወስዱት እርምጃ ሁለቱንም ልጆች መቅጣት ነው። ይሄ መንገድ አስተማሪ አይደለም። ችግሮች መፍቻ ተመራጭ መንገድም አይደለም። ምክንያቱም ሁልጊዜም የጸብ ምንጭ የሚሆነው ልጅ ራሱን የሚመለከትበት መንገድ የሰራው ትክክል እንደሆነ አድርጎ ነው። ስለዚህ ከስህተቱ አይማርም፤ በመነጋገር አያምንም፤ ይቅርታንም ወደ ልቡ አያስገባም። ስለዚህ ሁልጊዜም አበጣባጭና በጥባጭ ሆኖ ይቀጥላል።ስለዚህ ጥፋተኛ መሆኑን ላጠፋው ጥፋትም ይቅርታ መጠየቅ እንዳለበት ማስተማር ያስፈልጋል።

ከዚሁ ጎን ለጎንም ልጆች ለሰሩት መልካም ነገር፣ ላበረከቱት አስተዋጽኦ ሁልጊዜም ምስጋና ያስፈልጋቸዋል። ምስጋና የሰዎችን ሞራል ይገነባል። ለተሻለ ነገር ያበረታታል። በጓደኛሞች መካከል ጸብ ሲፈጠርና ሌላው ጓደኛውን አነጋግሮ ችግሮችን በመፍታት ይቅርታ እንዲጠያየቁ ካደረገ (ካደረጉ) አስታራቂን ማበረታታት ነገ ለሀገር ሰላም፣ ለህዝቦች ፍቅርና መተሳሰብ ግንባር ቀደም ተዋናይ ይሆናል። ስለዚህ ሁሉንም ነገር የተስተካከለ ለማድረግ መጀመሪያ መሰራት ያለበት በቤት ውስጥ በልጆች መካከል ፣በልጆችና በወላጆች ወይም በአሳዳጊዎች እንዲሁም በወላጆች መካከል አለመግባባቶች ሲፈጠሩ ቁጭ ብለው መነጋገር፣ ጥፋተኛውም ይቅርታ እንዲጠይቅና ተጎጂም ይቅርታ እንዲያደርግ ማድረግ ያስፈልጋል።ይሄ ለልጆቻችን የምናወርሰው አንዱ ሀብት መሆን አለበት።

«በአሁኑ ጊዜ መላው ህብረተሰብ በንግዱ ዘርፍ የሚስተዋሉ ሲ-ሥነምግባራዊ ድርጊቶችን ሲኮንንና ሲዋጋ ይገባል”

የግሉ ዘርፍ ለሀገሪቱ ኢኮኖሚ ዕድገት ከፍተኛ አስተዋፅኦ በማድረግ ላይ ይገኛል። ይሁንና ዘርፉ ከሥነ ምግባር ጉድለት፣ ከሙስና እና ብልሹ አሠራር ጋር በተያያዘ ስሙ እየተነሣ ይገኛል። ምንም እንኳን በግሉ ዘርፍ የተሠማሩ አብዛኞቹ የህብረተሰብ ክፍሎች ዘርፉ የሚጠይቀውን ሥነምግባር ተከትለው በመሥራት እራሳቸ ውንና ኅብረተሰቡን እያገለገሉ የሚገኙ ቢሆንም ጥቂቶቹ ግን መነሻና መድረ ሻቸውን ትርፍ ብቻ አድርገው ወዳል ተገባ አቅጣጫ ሲያመሩ ይታያል። በአንዳንድ ሥነምግባር በጎደላቸው አካላት ሌሎች ህገ-ወጥና ኢ-ሥነምግባራዊ ድርጊቶች እየተፈፀሙ ይገኛሉ። ከነዚህ መካከል በአሁኑ ጊዜ በዓለማችን ላይ ከፍተኛ አደጋ የደቀነውን የኮቪድ-19 (ኮሮና) ወረርሽኝን ምክንያት በማድረግ ሰው ሰራሽ የዕቃ እጥረት መፍጠር፣ በተለያዩ ምርቶች ላይ ባዕድ ነገሮችን መቀላቀል፣ ስውር በሆነ መልኩ በመነጋገር የዕቃዎችን ዋጋ ማናር እና ደንበኛን በአግባቡ ያለማስተናገድ የሥነምግባር ችግሮች እየተስተዋሉ ይገኛሉ። ይህ ዓይነት አካሄድ ወረርሽኙን ለመከላከል በሚደረገው ሁሉን አቀፍ ጥረት ላይ ብሎም በዜጎች ደህንነት ላይ መሰናክል እንደሚሆን ጥርጥር የለውም። በመሆኑም የንግዱ ማህ በረሰብ፣ መንግሥትና በአጠቃላይ መላው ህብረተሰብ ይህን ኢ-ሥነምግባራዊ ድርጊት ሊኮንንና ሊዋጋ ይገባል።

ስልክ ቁጥር፡- 011-552 77 79 00/ 011 552 77 85 ፋክስ፡- 011-553 69 89
011-557 77 86 ኢሜይል፡- feaccgov@yahoo.com ፖ.ሳ.ቁ፡- 34798/99
የፌዴራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን